# በረራ፤ የ፲፭ኛው ክፍለ ዘመንና የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነገሥታት ከተማ (ኢትዮጵያ)፤ በየረር ተራራና ወጨጫ ሸንተረሮች፤ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን እና ከዚያ ቀደም የነበረ የሕዝብ ሰፈራ፤ የቅርብ ጊዜ የምርምር ጥናቶች ውጤት፤

ሚስተር ሪቻርድ ፓንክኸርስትና ሚስተር ሐርትዊግ ብሬተርኒትዝ
አንዱዓለም ተፈራ ከእንግሊዝኛ ወደ ዐማርኛ እንደ ተረጎመው

**ማስታወሻ፤**

፩. በዚህ የትርጉም ጽሑፉ የተቀመጡት ዓመተ ምህረቶች በሙሉ፤ በተረጎምኩት ጽሑፍ በነበረው በአውሮፓዊያን አቆጣጠር ናቸው። የአውሮፓዊያን ዓመተ ምህረቶች፤ ከመስከረም እስከ ህዳር መጨረሻ ያሉት፤ ከኛው ዓመተ ምህረቶች የ፰ ዓመት ቅድሚያ ሲኖራቸው፤ ከጥር እስከ ጳጉሜ ያሉት ደግሞ ፯ ዓመት ይቀድማሉ።

፪. በተቻለኝ መጠን የዐማርኛ ቃላትን ብቻ ለመጠቀም ሞክሬያለሁ። አርኪዮሎጂ የሚለውን ቃል ብቻ፤ የጥንት የሰዎችን ታሪክና የተፈጥሮን ሁኔታ ምድርን ቆፍሮ በመመርመር ከግኝቶች ማጥናት የሚለው፤ የአንባቢን የግንዛቤ ፍስት ጨምድዶ ይይዛል በማለት፤ ሳልተረጉም እንዳለ አስቀምጨዋለሁ።

፫ ተጠቃሽ ማስረጃዎችን፤ ለመከተል ለሚፈልጉ ሰዎች፤ መነሻ ጽሑፉን የግድ ማግኘት ስላለባቸው፤ መተርጎሙን ጠቃሚ ሆኖ ስላላገኘሁት፤ እንዳለ አስቀምጨዋለሁ።

፬. መተርጎም የጀመርኩት ቀደም ብዬ ነበር፤ ነገር ግን ፈቃድ ከዶክተር አሉላ ፓንክኸርት ለማግኘት ስጠብቅ ብዙ ቆየሁ። አሁንም መልስ ስላልሠጡኝ፤ ጠቃሚነቱ ስላየለብኝና ለንግድ ሳይሆን በበጎ ፈቃደኝነት ለሕዝብ እንዲደርስ ለትምህርት ያደረግሁት በመሆኑ፤ ያለሳቸው ፈቃድ አድርጌዋለሁና፤ ከወዲሁ ይታወቅልኝ።

**ተርጓሚው - አንዱዓለም ተፈራ**

---

ይሄንን ሰነድ ስትጠቅሱ መስፈር ያለበት፤

ፓንክኸርስት፣ ሪቻርድ፤ ብሬተርኒትዝ፣ ሃርትዊግ፤ በረራ፤ የ፲፭ኛው ክፍለ ዘመንና የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነገሥታት ከተማ (ኢትዮጵያ)፤ በየረር ተራራና ወጨጫ ሸንተረሮች፤ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን እና ከዚያ ቀደም የነበረ የሕዝብ ሰፈራ፤ የቅርብ ጊዜ የምርምር ጥናቶች ውጤት

የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጥራዞች፤ ቅጽ ፳፬፣ ዓመተ ምህረቱ ፳፻፱፤ ገጽ ከ ፳፻፱ እስከ ፳፻፵፱

በተጻፈበት ቋንቋ በሙሉ ትክክለኛ አቀማመጡ የሚከተለው ነው።

Citer ce document / Cite this document :
Pankhurst Richard, Breternitz Hartwig. Barara, the Royal City of 15th and Early 16th Century (Ethiopia). Medieval and Other Early Settlements Between Wechecha Range and Mt Yerer: Results from a Recent Survey. In: Annales d'Ethiopie.
Volume 24, année 2009. pp. 209-249;

doi : 10.3406/ethio.2009.1394

http://www.persee.fr/doc/ethio_0066-2127_2009_num_24_1_1394

---

Document généré le 08/03/2018

## የጽሑፉ ጭምቅ ይዘት፤

በረራ፤ የ፲፭ኛው ክፍለ ዘመንና የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነገሥታት ከተማ (ኢትዮጵያ)፤ በየረር ተራራና ወጨጫ ሸንተረሮች፤ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን እና ከዚያ ቀደም የነበረ ሕዝብ ሰፈራ፤ የቅርብ ጊዜ የምርምር ጥናቶች ውጤት፤

ይህ ጽሑፍ፤ የበረራን እና በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን እና በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበሩ የሰፈራ ቦታዎችን ታሪክኅ ዞሮ ይመረምርና፤ ታሪካዊ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የሆነችውን በረራን፤ ቦታዋን ለይቶ፤ በደቡብ ሸዋ፤ በአሁኗ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፤ አዲስ አበባ ከተማ አቅራቢያ፤ መሆኗን ለማመላከት የታሰበውን የመስክ ጥናት ውጤቶችን ይገልጣል። ታሪካዊ ምንጮች እና የሳተላይት የጥልቀት ዕይታዎች፣ የመልክዐ ምድር አቀማመጥ ሁኔታዎች እና ተጨባጭ የአካባቢ መሬት ጥናቶች ላይ በመንተራስ፤ ደራሲዎቹ ወደኋላ ወደ ቅድመ መካከለኛው ክፍለ ዘመን የሚደርሱ የሚመስሉ አዳዲስ ቦታዎችን በማሳወቅ፤ ረጅሙን እና የኢትዮጵያ የዚህ አካባቢ እስካሁን ያልታወቀ ታሪክ አሳይተውናል። ሆኖም ግን፤ በረራን በትክክል ቦታው ላይ ማስቀመጡ አዳጋች ሆኗል። እናም የመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ የክርስቲያን "ከተሞች" ዕውቀታችን እንዲዳብርና እስካሁን በትክክል ያልተጠናውን ለሕዝቡና ለባህሉ እንቅስቃሴው ማዕከላዊ የሆነውን የዚህ አካባቢ የቅድመ መካከለኛው ዘመን ታሪክ እንዲገልጥልን፥ ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ።

BY: creative commons

የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጥራዞች ፳፻፱፣ ቅጽ ፳፬፣ ገጽ ፪፻፱ እስከ ፪፻፵፱

# በረራ፤ የ፲፭ኛው ክፍለ ዘመንና የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነገሥታት ከተማ (ኢትዮጵያ)፤

## በየረር ተራራና ወጨጫ ሸንተረሮች፤ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን እና ከዚያ በፊት የነበረ የሕዝብ ሰፈራ፤ የቅርብ ጊዜ የምርምር ጥናቶች ውጤት

ሐርትዊግ ብሬተርኒትዝ እና ሪቻርድ ፓንክኸርስት [፩]

************

## የጽሑፉ ጭምቅ ይዘት

ይህ ጽሑፍ፤ የበረራን እና በ፲ ፭ኛው ክፍለ ዘመን እና በ፲ ፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበሩ የሰፈራ ቦታዎችን ታሪክን ዞሮ ይመረምርና፤ ታሪካዊ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የሆነችውን በረራን፤ ቦታዋን ለይቶ፤ በደቡብ ሸዋ፤ በአሁኗ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፤ አዲስ አበባ ከተማ አቅራቢያ፤ መሆኗን ለማመላከት የታሰበውን የመስክ ጥናት ውጤቶችን ይገልጣል። ታሪካዊ ምንጮች እና የሳተላይት የጥልቀት ዕይታዎች፣ የመልክዐ ምድር አቀማመጥ ሁኔታዎች እና ተጨባጭ የአካባቢ መሬት ጥናቶች ላይ በመንተራስ፤ ደራሲዎቹ ወደኋላ ወደ ቅድመ መካከለኛው ክፍለ ዘመን የሚደርሱ የሚመስሉ አዳዲስ ቦታዎችን በማሳወቅ፤ ረጅሙን እና የኢትዮጵያ የዚህ አካባቢ አስካሁን ያልታወቀ ታሪክ አሳይተውናል። ሆኖም ግን፤ በረራን በትክክል ቦታው ላይ ማስቀመጡ አዳጋች ሆኗል። እናም የመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ የክርስቲያን "ከተሞች" ዕውቀታችን እንዲዳብርና እስካሁን በትክክል ያልተጠናውን ለሕዝቡና ለባህሉ እንቅስቃሴው ማዕከላዊ የሆነውን የዚህ አካባቢ የቅድመ መካከለኛው ዘመን ታሪክ እንዲገልጥልን፥ ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ።

ቁልፍ ቃላት፤ ኢትዮጵያ፣ ሸዋ፣ አርኪዎሎጂ፣ ታሪክ፣ የመካከለኛው ክፍል ዘመን ከተሞች

---

**፩** ሐርትዊግ ብሬተርኒትዝ ( Hartwig.Breternitz@googlemail.com ) ቅድመ-ታሪክ፣ የግብርና ማጣኔ-ሀብት፣ እና የሕዝብ አስተዳደርን ዕድገት አጥንተዋል። ከ፳፻፫ ዓመት ምህረት እስከ ፳፻፱ ዓመት ምህረት ድረስ በአዲስ አበባ፤ የአፍሪካ ኅብረት አንድነትን፤ በዘለቄታ የአስተዳደር ጉዳዮች አማክረዋል። ከዚያ ወዲህ በደቡብ ሸዋ ታሪክ ፍቅር አድሮባቸው፤ ከፕሮፌሰር ፓንክኸርስት ጋርም በቅርብ በመተባበር፤ በአዲስ አበባ ዙሪያ የመስክ ጥናቶችን አካሂደዋል።

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ኬ. ፒ. ፓንክኸርስት ( pankhurst@ethionet.et ) የታሪክ ምሁር፣ በ፲፱፻፶፮ ዓመት ምህረት ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። ከዚያ ለረጅም ጊዜ የሙያ ጊዜያቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር በመሆን አገልግለዋል። እሳቸው በ፲፱፻፷፫ ዓመት ምህረት እዚያው የኢትዮጵያ ጥናት ተቋምን መሥርተው የመጀመሪያው ርዕሰ-ተቋም ነበሩ። ፕሮፌሰር ፓንክኸርስት ብዙ የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል መጽሐፍትንና የጥናት ጽሑፎችን ደርሰዋል። ለረጅም ዓመታት የኢትዮጵያ ጥናቶች መጽሔት እና የታዛቢ ኢትዮጵያ የጋራ አዘጋጅ ነበሩ። ደራሲዎቹ፤ ፍራንስዋ-ዣቪየር ፈውቢሌ-አይማር እና ክሌር-ቴይሴን፤ ከየፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል ( CFEE )፤ የጥናት ምርምሩን በማካሄድና ጠቃሚ ጥቆማዎች በመሥጠት ላደረጉላቸው ድጋፍ ያመሰግኗቸዋል።

የኢትዮጵያ ልዑላን ወግ አብላጫ ገጽታው፤ የንገሡ ነገሥቱ መቀመጫ፤ በቋሚነት ተለዋዋጭ መሆኑ ነበር። የዚህን በተሻለ መንገድ ግንዛቤ የደረስንበት፤ አሁን በያዝነው ሺኛ ዘመን መጀመሪያ ወዲህ ብቻ ነው።[፪] ሆኖም ግን፤ "ተንቀሳቃሽ ዋና ከተማዎች" እና ጎልተው የደመቁ የልዑላን የሰፈራ ቦታዎች፤ በተለይም በሸዋ፤ ከሌሎች የዐማራ አካባቢዎች ቀጥሎ፤ ከ ፲፫ ኛው እስከ ፲፮ ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ[፫] ነበሩ። ከነኚህ አንዷ፤ በረራ፤ በደቡብ ምሥራቅ ሸዋ የሰፈራ ቦታ፤ አንድ ክፍለ ዘመን ሊሞላው የተጠጋ ጊዜ ዋና ከተማ የነበረች ትመስላለች። የ፲፭ ኛው እስና የ፲፮ ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዋ ኢትዮጵያ፤ የፖለቲካና የምጣኔ ሀብት ሆና ማገልገሏ ግልጽ ሆኖ እያለ፤ የሀገሪቱ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ብቻ የምትታወቅ እናም ፍጹም ሚስጥር የሆነች ከተማ ናት። ሆኖም ግን፤ ግራኝ እየተባሉ በተለምዶ በሚታወቁት፤ የአፋሩ ጦረኛ አሚር አሕመድ ቢን ኢብራሒም ከተወረረች በኋላ፤ በ፲፮ ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ፤ ከተማዋና ቀሪው ጠቅላላ ደቡብ ሸዋ፤ ከሌላ ቦታ በመጡ ኦሮሞዎች መቀመጫ ሆኑ። ከዚህም የተነሳ፤ ስለ በረራና ሌሎች ታሪካዊ ቦታዎች መታወቃቸው ጠፋ።

ደመቅ ያሉ ቋሚ የመካከለኛው ዘመን የሙስሊሞች ከተሞች፤ ገና በቅርብ በይፋት አካባቢ መኖራቸው ታውቆ፤ ተቆፍረዋል።[፬] በክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን የንጉሥ ነገሥት ግዛት ክልል፤ ቋሚ የሆኑ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን "ከተሞች" አልተገኙም። ለኢትዮጵያ ታሪክ፤ ባጠቃላይ ግንዛቤው፤ ከተማን መሰል ቋሚ የታነጹ ቦታዎች፤ አንድም አልነበሩም ወይንም ወሳኝ ያይደሉ ናቸው ተብሎ ተወስዷል። ከዚህም የተነሳ፤ ስለነዚህ የተዘነጉ የነገሥታት መቀመጫዎች፤ ምን ይመስሉ እንደነበር፣ ግዝፈታቸውና ምን ያህል ተፈላጊ እንደነበሩ፤ ምንም ዓይነት መረጃ የለንም። እኒህን የመሰሉ ከተሞች መኖራቸውን ከሚያመለክተው የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ዝርዝር በቂ ምንጮች አንጻር፤ አስገራሚ ነው። በረራ፤ ከዛሬዋ ዋና ከተማ፤ ከአዲስ አበባ ካለችበት አካባቢ ከነበሩ ሌሎች ከተሞች ጋር፤ በግልጥ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የኅብረተሰቡ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። እናም የበረራንና የሌሎች የነገሥታት መቀመጫ ቦታዎችን ትክክለኛ ስፍራ ማፈላለግ፤ የዚህ የጥናት ሰነድ ግብ ነው።

የመካከለኛው ዘመን ምንጮች፤ አንጥረው በማውጣት ቦታውን ሳያሳዩ፤ የበረራን አካባቢ በሚመለከት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ጥቆማቸውን አስፍረዋል። ከሞላ ጎደል፤ በምዕራብ በኩል በወጨጫ አግድም ተራሮችና[፭] በአቃቂ ወንዝ መካከል፤ በሰሜን የረር ተራራ፣ በደቡብ ዝቋላ ተራራና የአዋሽ ወንዝ፣ በምሥራቅ ደግሞ የሞጆ ወንዝ/ደብረዘይት አካባቢ ለማስቀመጥ በቂ መረጃ አለ። ይህ፤ ከአሁኗ አዲስ አበባ፤ ደቡብ/ደቡባዊ ምሥራቅ፤ በግምት ፶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ አካባቢ ነው። ይህ ደግሞ፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ የዱከም ወንዝ ሲፈስ ማዕከላዊ ክፍሉን ያቋርጠዋል ማለት ነው። (**ስዕል ፩ን ይመልከቱ** )

---

፪ ቢ. ሂርሽ እና ቢ. ፖይዞነር ( ፳፻ ) B. HIRSCH & B. POISSONNIER (2000)

፫ ኤም. ኤል. ደራት ( ፳፻፫ ) M.-L. DERAT (2003) ለ ፲፫ አስከ ፲፮ ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት፤ የአማራ ቦታና የሸዋ ክፍልን፣ የነገሥታቱ "ዋና ከተሞች" እና ብዛት ያላቸው ቤተክርስትያናትና ገዳማት ሚና ለሃይማኖት አገልግሎትና ለአካባቢያቸው የፖለቲካ ሂደት ምን ያህል ዋና አስፈላጊ እንደነበሩ በዝርዝር ገልጠውታል። በእርሻ ሀብት ምንጭነታቸው፤ በተለይ ሸዋ፤ የፖለቲካውና የምጣኔ ሀብቱ የዚያ ወቅት የኢትዮጵያ ዋና አካባቢ ሆኗል (ከማሁ ገጽ ፵፭ - ፵፱ ) (*ibid.*, 45-49).

፬ ኤፍ. ኤክስ. ፎቪል-አይማር እና ሌሎች ( ፳፻፮ ገጽ ፻፴፫ - ፻፸፭) F.-X. FAUVELLE-AYMAR *et al.* (2006: 133-175).

፭ በዚህ ጽሑፍ፤ ፩ ለ ፶ሺህ ውክልና ላለበት የኢትዮጵያ ካርታ ቀራጭ ድርጅት (ኢካቀድ) ከ ፲፱፻፸፫ ጀምሮ የዋለውን፤ ( Ethiopian Mapping Agency (EMA) since 1973. ) ተጠቅመናል

ይህ የጽሑፍ ዘገባ፤ የዚህ አካባቢ የመስክ ጥናት ውጤት ነው። በዚህ አካባቢ፤ የበረራንና ሌሎች የነገሥታት መቀመጫዎችን ለይቶ ማመላከት፤ የዚህ የጥናት ዘገባ ዓላማ ነው። በተጨማሪ፤ ጥናቱ፤ በአካባቢው ያሉ ታሪካዊ ቦታዎች ላይ ገጽታውን በማሳየት፤ ተጨባጭ ግንዛቤ ለመሥጠት ጥሯል። እናም ከ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ከመውደማቸው በፊት፤ በመካከለኛው ዘመን ቦታዎችና አሰፋፈር ለነበረን ዕውቀታችን አስተዋፅዖ አድርጓል።

## ደቡብ ሸዋ በ፲ ፫ኛውና ፲ ፮ኛው ክፍለ ዘመንና ተዛማጅ የአርኪዮሎጂ መረጃዎች

ምንም እንኳን አንጻራዊ በሆነ መንገድ ብዙ ታሪካዊ ምንጮች ( መዋዕለ ዜናዎች፣ የተጓዦች ዘገባዎች፣ ወ.ዘ.ተ. ) ከመካከለኛው ዘመን የአርኪዮሎጂ መረጃዎች ቢኖሩም፤ በዚህ ዘመን ላይ የተደረጉ ምርምር እና ጥናቶች በውል አያመረቁም። በአክሱም ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ( ፰ኛው ክፍለ ዘመን ) እና የኢትዮጵያ ታሪክ “ፊቱን ያዞረበት ሰዓት” - በ፲ ፮ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ በአሕመድ ግራኝ መወረር - መካከል ያሉት የቁስ ማስረጃዎች በጣም ውስን ናቸው።

ይህ በግልጥ፤ ሸዋ፤ በተለይም ደቡባዊ ክፍሉ ከነበረው ከፍተኛ ታሪካዊ ይዞታ ጋር ተጓድኖ ሲነጻጸር፤ ላይና ታች ነው። በአካባቢው ላይ የተደረገው የመካከለኛው ዘመን የአርኪዮሎጂ ጥናት፤ በጣም አነስተኛ በሆኑ ስፍራዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፤ የሶዶ አካባቢ (ቲያ) ሐውልት ዕነጻ ባህል፣ በመካከለኛው ዘመን ነበር ተብሎ የሚታመነው፤ ከወጨጫ የተራራ ሰንሰለቶች ሰሜን በኩል፤ በመናገሻ ተራራ የኢትዮጵያን ነገሥታት የማንገሥ ስነ ሥርዓት ባህል፣ በአፄ ዘረ ያዕቆብ የተጀመረው፤ ( የንግሥና ዘመናቸው ከ ፲፬፻፴፬ እስከ ፲፬፻፷፰ ዓመተ ምህረት ድረስ ) የመናገሻን ደን ( የወጨጫ የተራራ ሰንሰለት ደቡባዊ ቁልቁለት ) ነገሥታቱ ጥበቃ መሥጠታቸው፣ በ፲፪ናው ክፍለ ዘመን የተቆረቆረው በዝቋላ ተራራ የሚገኘው ገዳም፣ እና በመጨረሻም፤ ከሌሎች ያነሰ ክብደት የሌለው፤ ካንዱ አንዱ ተያይዘው በነገሥታቱ የተቆረቆሩት ቤተክርስትያናት፤ ( እንስላሌ፣ ግንቢ፣ ኤጀርሳ፣ እና ሌሎች ) ናቸው። አብዛኛዎቹ ምናልባትም በ፲፫ኛና በ፲ ፮ኛው ክፍለ ዘመን የተቆረቆሩ ናቸው። እኒህ በደቡብ ሸዋ፤ በ፲ ፱ ፻ ፷ ዋቹና በ፲ ፱ ፻ ፸ ዋቹ ክፍለ ዘመናት፤ [፩] በተጨማሪም በቅርቡ የተገኙ ናቸው። [፪]

የነገሥታት መስፈሪያ ቦታዎች መኖራቸውን ታሪካዊ ጽሑፎች ዘግበዋል። በዛ ያሉ የኢትዮጵያ ገዥዎች ቋሚ ዋና ከተማ ለቆርቆር ሞክረዋል። እኒህ ተመሥርተው፤ በንጉሡ በተደጋጋሚ ተጎብኝተዋል።

---

፩ እንደ ኤም. ኤል. ደራት ጥናት፤( ፳፻፫፤ ገጽ ፳፻፱ ) M.-L. DERAT (2003: 209), የኢትዮጵያ ነገሥታት፤ ከ፲፫ኛው እስከ ፲፮ኛው ክፍለ ዘመናት ድረስ፤ ፴፬ ቤተ ክርስትያናትና ገዳማትን መሥርተዋል። ከነኝህ አብላጫዎቹ በ፲፫ኛና በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የተቆረቆሩ ናቸው።

፪ ኤፍ. አንፍሬይ ሲያትት፤ ( ፲፱፻፸፰፤ ገጽ ከ፻፶፫ እስከ ፻፷፱ ) F. ANFRAY (1978: 153-169). አሁን በቅርብ ጊዜ ለአዲስ አበባ በስተ ምሥራቅ በኩል ቅርብ በሆነ አካባቢ ( ገርጂ )፤ ያካባቢው ነዋሪዎች አንድ ኮረብታ ሲቆፍሩ፤ የቀድሞ ሕንፃ ፍርስራሽ አገኙ። ይህ ፍርስራሽ፤ አቅጣጫው (8o 59’24”N, 38o 50’60”E) (Gerji) (8o 59’ 24” N, 38o 50’ 60” E): በሆነ ቦታ ሲገኝ፤ ሕንፃውን ሲገኝ፤ ( መሠረቱ፤ ፲ ሜትር በ ፲ ሜትር አራት ማዕዘን ኖሮት፤ በዚያው ቦታ ግንበኞች የዋሉበት፣ የሸክላ ስብርባሪዎች፣ በስነ ሥርዓት የተቀበሩ አጽሞች አብረው ተገኝተዋል። ) (rectangular foundation, ca. 10x10 m, masonry work, pottery, bones from burials) ያገኙት ሰዎች፤ ሕንፃውን የቤተክርስትያን ፍርስራሽ ነው በማለት ወስደውታል። በዚህ በፍርስራሹ መሠረት ላይ፤ አዲስ ቤተ ክርስትያን፤ የረር ሥላሴ ታንፆበታል። ግምበኞቹ የተጠቀሙበት አሠራር እና በቤተክርስትያኑ ዙርያ በተገኙ ቁሳቁሶች ላይ የዋለው ዕደ ጥበብ ( የግምብ አሠራር ጠበቦች፣ ሸክላዎች ) በሌሎች አካባቢዎች ከተገኙ የቅድመ-ግራኝ ቤተክርስትያኖች ጋር ተመሳሳይነት አሳይተዋል። ይህ ደግሞ፤ በርግጥም ግራኝ ከመምጣቱ በፊት በደቡብ ሸዋ፤ በነገሥታቱ ተያይዘው ከተሠሩት የሃይማኖት ቦታዎች አንዱ ቤተክርስትያን እንደሆነ ያመለክታል።

በተለይ በሸዋ፤ ከኒህ የመስፈሪያ ቦታዎች መካከል፤ አንዳንዶቹ ገናና ሆኑ ( ደብረ ብርሃን፣ በረራ፣ ባደቀ )። የኢትዮጵያ ነገሥታት በኒህ "ከተሞች" ባለሙያ እጀ ጥበበኞችን ያበረታቱና ይደግፏቸው ነበር ( ለምሳሌ፤ በባደቀ፤ የንጉሡ አልባሳት ጠቃሚዎች )። ሆኖም ግን፤ በጊዜው የነበሩ መጠነ ሰፊ ዘገባዎች እያሉም፤ በኢትዮጵያ የመካከለኛው ዘመን የክርስትያን ከተማ ምን ይመስል እንደነበር ያለን ዕውቀት፤ በአውሮፓዊያን የከተሞችና ዋና ከተሞች ግንዛቤ ውስንና የተዛባ ነው። [፰]

የዚህ ቋሚ የሆነ የመካከለኛው ዘመን የክርስትያን መስፈሪያ ቦታዎች ዕውቀት ማጣት፤ በታሪክ አዋቂዎች ዘንድ በሰፊው ተቀባይነት ያገኘውን ፅንሰ-ሃሳብ፤ በኢትዮጵያ ቋሚ የሰፈራ ዋና ከተማዎች ፍጹም እንደሌሉ አድርጎ መገመትን አስከተለ። [፱] የቅርብ ጊዜ ምርምር፤ ተሰውሮብን የነበረውን የኢትዮጵያ ነገሥታት "እግር ያወጣ ዋና ከተማ" የመጀመሪያውን የአርኪዎሎጂ መረጃ አስገኝቶልናል። [፲] ከ፲፫ኛው እስከ ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን በነበሩት የነገሥታት መስፈሪያ ቦታዎች ላይ የሚጨበጡ መረጃዎች ወደፊት ይገለጣሉ።

## በረራና ደቡብ ሸዋ በፍራ ማውሮ የ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ካርታ

የበረራ ሕልው መሆን መጀመሪያው ፍንጩ የተገኘው፤ ቬኒስ ላይ በ፲፬፻፶፬ ዓመተ ምህረት የቬኒሱ ካርታ ቀራጭ ፍራ ማውሮ ባወጡት ስመ ጥሩ የዓለም ካርታ ላይ ነው። በአውሮፓ ተቃኝቶ በተገኘው መረጃ መሠረት፤ የኢትዮጵያው ክፍል፤ ትክክለኛውን የመልክዐ ምድር ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ይመስላል። ከዚያ ላይ "በረራ" የሚል ቦታ ያመለክታል። ቦታውን፤ የቤተመንግሥት ወይንም የግንብ ስፍራ ተብሎ ተመላክቷል። ቦታው፤ በዶኮ እና በአውሲ ወንዞች፤ የዛሬዎቹ የዱከምና የአዋሽ ወንዞች መካከል ተቀምጧል። በትኩረት ደግሞ ከዱከም ምዕራብና ከአዋሽ ሰሜን ነው። [፲፩] ካርታው፤ ከዱከም ወንዝ ወዲያ፤ ይህም ማለት፤ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ርቆ፤ "ዝቋላ" የሚባል ተራራ፤ "ትልቅ ሐይቅ ያለበትና የባህታዊያን ደብር በማለት፤ ያለምንም ጥያቄ የዛሬውን የዝቋላ ተራራ፤ ከዕድሜ ጠገብ ገዳሚና ሐይቋ ጋር በማያወላውል ሁኔታ አረጋግጦ አመላክቷል። ፍራ ማውሮ፤ ዝርዝር መረጃውን ከማን እንዳገኙት ግልጽ አይደለም፤ ይሁን እንጂ፤ በተለየ ሁኔታ መልክዐ ምድሩን በትክክል ማስቀመጣቸው፤ ወደዚያ ቦታ ለመሳለም የሚጓዙ ኢትዮጵያዊያን ወይንም ሸዋን በተለይም ዝቋላን የሚያውቁ መነኮሳት እንደሆኑ ይጠቁማል።

ከዱከም ምዕራብ የሚገኘውና ፈሶ ወደ አዋሽ የሚገባው የአቃቂ ወንዝ፤ ከዱከም እጅግ የጠነከረ ሆኖ እያለ፤ በግልጽ በካርታውም አልተካተተም። የዱከም ወንዝ የዓመቱን አብላጫ ወራት ሙሉ ለሙሉ ይደርቃል። ሆኖም ግን፣ በስተምሥራቅ በኩል፤ ካርታው፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ ሄዶ ወደ አዋሽ የሚገባ፤ ከወደ አናቱ ሜሶን የምትባል ከተማ የምትገኝበት፤ ሌላ ወንዝ ያሳያል። ይሄንን ወንዝ፤ ከሞላ ጎደል የሞጆ

፰ ኤም. ኤል. ድራት ( የ፳፻፫ ዕትሙ ምዕራፍ ፩ ) M.-L. DERAT (2003, chap. 1).

፱ አር. ፓንክኸርስት ( የ፲፱፻፷ ዕትሙ ገጽ ፻፴፯ እስከ ፻፵፪ ) R. PANKHURST (1960: 137-142).

፲ ከደብረብርሃን ቅርብ ከሆነው መንዝ ውስጥ የተቆፈረው በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ነገሥታት የሰፈሩበት ቦታ፤ በግልጽ የ "እግር ያላቸው ዋና ከተማዎች" ባህሪ የሆነው፤ አንጻራዊ ስፋት ያለው፤ ነገር ግን በቀላሉ ሊለቀቅ የሚችል የአሰፋፈርና የመኖሪያ አሰራር ሁኔታ አሳይቷል። ( ቢ. ሂርሽ እና ቢ. ፖይዞኒይር፣ ፳፻ ገጽ ከ፶፱ እስከ ፹፯ ) (B. HIRSCH & B. POISSONNIER, 2000: 59-87)

፲፩ በገጽ ፲፱ የሰፈረው፤ እንደገና ተሠርቶ የተቀመጠው ካርታ በረራን ከዱከም በስተምሥራቅ ያሳያል። ፊት ለፊት በተቀመጠው በገጽ ፳ የተካተተው በምዕራብ ያሳያያል። ይሄኛው በግልጥ፤ በ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድም (፲፱፻፶፰ ዓመተ ምህረት የተጻፈ፤ ገጽ ፲፱ እስከ ፳፤ በግምት ከ ፲፬፻ እስከ ፲፭፻፳፬ ዓ. ም.) ከተቀመጠው ከዋናው ካርታ ጋር ከተነጻጸረ ትክክለኛ ቅጅ ነው። O.G.S. CRAWFORD (1958: 19-20, circa 1400-1524).

ወንዝ [፲፪] ነው ብሎ መገመት ይቻላል። ሌላው ዋና ጎኑ፤ ከበረራ ምዕራብ የተቀመጠው የአምባነገሥት ሌላው ዋና ጎኑ፤ ከበረራ ምዕራብ የተቀመጠው የአምባነገሥት ተራራ፤ ማለትም የነገሥታት ተራራ ነው። በዋናው የፍራ ማውሮ ካርታ፤ አምባነገሥት የ "ርዕሰ-ባለቤቱ መኖሪያ" ተራራ ነው የሚል ማስታወሻ ይነግረናል። ( **ስዕል ፪ን ይመለከቱ** )

## የዞርዚ የጉዞ ዘገባና ሌሎች የመካከለኛው ዘመን ምንጮች በበረራና በሌሎች በአካባቢው የመካከለኛው ዘመን የነገሥታት "መንደሮች" ላይ

በ፲፬፻፸፬ ዓ. ም.፣ የፍራ ማውሮ ካርታ ከወጣ በኋላ፣ የቬኒሺያው የጽሑፍ ምሁር፣ ከኢትዮጵያ በቅርብ ደርሰው የተመለሱ ጣሊያናዊ መነኩሴ ጋር ተገናኙ። ማንነታቸው ያልታወቀው እኒህ መነኩሴ፤ በአውሮፓ፤ አውሮፓዊያኑ በዚያን ጊዜ ለነበሩት የኢትዮጵያዊያን ነገሥታት በሠጧቸው ስም፤ የካህኑና የንጉሡ ዮሐንስ፤ ( የፕሬስተር ጆን ) ዋና ከተማ፤ በረራ ተብላ ትጠራለች፤ በአጎራባች አውራጃዎቿ፤ "የማር ከምችት ቦታ" አለ ብለው ነግረዋቸዋል። [፲፫]

በረራ ምን ያህል ዋና ቦታ እንደነበረች፤ ያን ወቅት ተከትሎ፤ በጣሊያናዊው ሀገር ጎብኚ፤ በፍራንሲስኮ ሱሪያኖ የጉዟቸው ዘገባ ማረጋገጫ ተመዝግቧል። [፲፬] እሳቸው፤ በ፲፬፻፹፪ ዓ. ም.፣ ከካይሮ ተነስተው እስከ፤ በሳቸው አገላለጽ፤ "በረራ ተብሎ በሚጠራው ቦታ፤ የታላቁ ንጉሥ፤ የካህኑና ንጉሡ ዮሐንስ ግቢ፤" ድረስ መጓዛቸውን አውስተዋል።

ስለበረራ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ፤ ከላይ የተጠቀሱት ደራሲ፤ አሌክሳንድሮ ዞርሲ፤ በጣልያን የሚገኙ ኢትዮጵያዊ የቤተ ክህነት ሰዋችን ሆን ብለው በትጋት በማፈላለግና ቃለ ጥያቄዎችን በማድረግ፤ ብዙም ባልራቀ ጊዜ ውስጥ፤ መረጃዎችን ሰብስበዋል። በቃለ መጠይቃቸው፤ እኒህን የቤተ ክህነት ሰዋች፤ ስለሀገራቸውና ስለ መልክዐ ምድሯ፤ አጥብቀው ጠይቀዋቸዋል። ዞርሲ፤ የተለዬ ትኩረታቸው፤ የተጓዦችን የጉዞ ዘገባ መዘገብ ሲሆን፤ አስከትሎም ከኢትዮጵያዊያኑ ያገኙትን መረጃ መዘገብ ነበር። ለበረራ ሕልውና፤ ዋና ቦታ በመሥጠት በኩል፤ መረጃውን ከሠጡት ኢትዮጵያዊያኑ ካህናት መካከል፤ ሁለቱ (ሩፋዔልና ቶማስ) ከዚያው ከበረራ አካባቢ የመጡ መሆናቸው፤ ደግሞም ከስድስቱ የቬኒሺያ የጉዞ ዘገባዎች ውስጥ፤ ሶስቱ ከዚያው ከቬኒሺያ መነሳታቸውና አንደኛው እዚያው መጨረሻቸው መሆኑ፤ ትልቅ ቁም ነገሩ ነው።

በተጨማሪም፤ አራት ኢትዮጵያዊ መነኮሳት፤ ወንድማማቾቹ፤ ኒኮላስ፣ ዞርጊ (ምናልባት ዞርጋው)፣ ሩፋዔልና ቶማስ፤ ላጭር ጊዜ ቢሆንም፤ ዞርሲን ስለ በረራ "ከተማ" ነግረዋቸዋል። እነሱም፤ አንድ በሆነ ቃል፤ የንጉሥ ነገሥት ልብነ ድንግል፤ ( የንግሥና ዘመናቸው፤ ከ ፲፭፻፳ እስከ ፲፭፻፴ ድረስ )፤ ዞርሲ ፕሬስተር እና አቡን ወይንም ርዕሰ-ደብር ብለው የዘገቧቸው፤ ዋና መቀመጫ ቦታ ናት ሲሉ ገልጠዋታል። አባ ሩፋዔል ስለ ሰፈራው ቦታ፤ በጣም አጭሩን ዝርዝር ሠጡ። ዞርሲ፤ የፕሬስተር [፲፭] "ዋና ከተማ" ናት ብለውኛል በማለት ይጠቅሷቸዋል። አባ ኒኮላስ በበኩላቸው፤ በተመሳሳይ ሁኔታ የንጉሡና አቡኑ "ዋና ከተማ" ናት በማለት፤

---

፲፪ በፍራ ማውሮ ካርታ እንደተመለከተው፤ ከዱከም በስተምሥራቅ የሚገኝ፤ ከሰሜን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ፈሶ ወደ አዋሽ ወንዝ የሚቀላቀለው፤ ሞጆ ብቻ ነው። በስተምሥራቅ ራቅ ብሎ፤ ወንዞች አቅጣጫቸውን ለውጠው፤ በቀጥታ ወደ ሰሜን ምሥራቅ በመፍሰስ፤ አዋሽን ቆየት ብለው በርቀት ላይ ይደርሱበታል።

፲፫ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ገጽ ፻፳፯ ) O.G.S. CRAWFORD (1958: 127).

፲፬ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ገጽ ፵፬ ) O.G.S. CRAWFORD (1958: 44).

፲፭ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ከገጽ ፻፴፰ - ፻፴፱ ) O.G.S. CRAWFORD (1958: 138-139).

ነገር ግን፤ አቡኑ [፲፮] ባለቤት የሆኑበት “ግምብ”ም አለበት፤ በማለት ተናግረዋል። አባ ዞርጊ (ምናልባት ዘርጋው)፣ ሰፋ አድርገው በመግለጥ፤ በረራን፤ የንጉሥና አቡኑ “ዋና ከተማ”፣ ሞቅ ያለችና ሁሉ የሚገናኝባት፤ ንጉሠ ነገሥቱ “አብዛኛውን ጊዜያቸውን” የሚቀመጡባት በማለት ገልጠዋታል። በተጨማሪም እሳቸው፤ ርዕሰ-መንግሥቱ በዚያ ቦታ ግዙፍ “ግምብ” አላቸው ሲሉ ተናግረዋል። [፲፯] የጋንገቱ አባ ቶማስ፤ ከላይ የተጠቀሱት ካህናት የተናገሩትን ትክክለኛ ነው በማለት አስተጋብተዋል። እሳቸው በረራን፤ “ታላቅ ከተማ” እና የርዕሰ-ባላባቱ “ትልቅ ቤተክርስቲያን” ያለባት በማለት ገልጠዋታል። [፲፰]

ከላይ ያለው መረጃ፤ ቀደም ብሎ በተጠቀሱት አባ ቶማስ እና ሌላው የዞርሲ አስረጂ በሆኑት በአባ አንቶኒዮ ተጨማሪ ማስረጃዎች ዳብሯል። [፲፱] ሁለቱም ካህናት፤ በረራ “የወይና ደጋ” አየር ጠባይ አላት በማለት ገልጠዋል። ይህ፤ እንደ አብዛኛዎቹ ሞቅ ያሉ የኢትዮጵያዊያን የሰፈራ ቦታዎች፤ ከምድር በላይ ከፍ ያለ ቦታ ላይ እንደነበረች ያመለክታል። ይሄ እንዳለ ሆኖ፤ ስመ ጥሩ ፖርቹጋላዊ ጎብኚ፤ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ፤ በረራን ያልጠቀሰ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህም በዚያም ቢሆን፤ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ ከንጉሡ ጋር ለመገናኘት፤ ከተማዎን የመጎብኘት ዕድሉ በጣም የሰፋ ነው።

በረራ አቀማመጧ በሀገሪቱ ደቡባዊ ምሥራቅ ክፍል ከመሆኑ የተነሳ፤ በአሕመድ ኢብን ኢብራሂም የጦር ኃይል፤ ከመጀመሪያዎቹ ተጠቂ የመኖሪያ ሰፈሮች መካከል አንዷ እናም መስፈሪያቸው ሆናለች። ይህ በ ፲፭፻፴ ዓ. ም. አካባቢ የተከናወነው ክስተት፤ በየመናዊው የግራኝ የግል ዋና ዘጋቢ፤ አረብ ፋቂ፤ ፋቱህ አል ሐበሽ፣ ወይንም የአቢሲኒያ ወረራ በሚለው ተመዝግቧል። ይሄ ቀደም ብሎ የተገለጠውን የበረራን ከፍ ያለ ሰፍራ የነበራት መሆኑን ያረጋግጣል። [፳]

አረብ ፋቂህ የግራኝን የአካባቢውን ዘመቻ ሲገልጥ፤ “ከበረራ አናት ላይ” እንደ ደርሰ፤ የቀድሞው ንጉሠ ነገሥት ናዖድ ( የንግሥና ዘመናቸው ከ ፲፬፻፺፬ እስከ ፲፭፻፰ ድረስ ) ካሳነጹት አንድ ሀብታም ቤተክርስትያን እግር ጣለው። የቤተክርስትያኑን አያሌ ሀብትና የእስልምና ተከታይ ወታደሮቹ እንዴት እንደዘረፉት በማስታወስ፤ አረብ ፋቂህ ይቀጥላል፤ [፳፩]

“የአስልምና ተከታዮቹ ከቤተክርስትያኑ ሲደርሱ፤ ከወርቅና ከብር በተሠሩ ገበታዎች ታጭቆ አገኙት። የወርቅ ሳህኖች፣ የወርቅና የብር ገበታዎች እና የሐር መጋረጃዎች ነበሩ። እነሱ ( የግራኝ ታጣቂዎች ) እጅግ ብዙ ዕቃ ዘርፈው ወሰዱ ( . . . )። የእስልምና ተከታዮቹ ብዙ ዕቃዎችን ዘርፈው አካበቱ። በሃያ ቀናት ውስጥ፤ ( እነሱ ) በቁጥር ያልተገለጠ ወርቅ፣ ብርና የሐር ጨርቅ ዘረፉ ( . . . )።

---

፲፮ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ከገጽ ፻፲ - ፻፲፩፣ ፻፳ - ፻፳፩ ) O.G.S. CRAWFORD (1958: 110-111, 120-121).

፲፯ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ከገጽ ፻፴፪ - ፻፴፫ ) O.G.S. CRAWFORD (1958: 132-133).

፲፰ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ከገጽ ፻፵፰ - ፻፵፱፣ ፻፶፮ - ፻፶፯) O.G.S. CRAWFORD (1958: 148-149, 156-157).

፲፱ ኦ. ጂ. ኤስ. ክራውፎርድ ( በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ከገጽ ፻፸፫ - ፻፸፬ ) O.G.S. CRAWFORD (1958: 173-174).

፳ በርግጥ ባረራ ወይንም ባራራ፤ በዚህ ምንጭ በእንግሊዝኛው የቃላት አቀማመጡ፤ በፋቱህ አል ሃበሽ፤ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የተጠቀሰችው። ሆኖም ግን፤ ሌላ የልዑላን መንደር፤ በዘገባው ተደጋግማ የተጠቀሰችው በረራ፤ ከባረራ/ባራራ ጋር ከሞላ ጎደል አንድ ናት ( ኤም. -ኤል. ደራት፣ ፳፻፫ ዓ. ም. ገጽ ፵፰ ) (ላንባቢ እንዲረዳ የእንግሊዝኛውን የግርጌ ማስታወሻ እንዳለ አስቀምጨዋለሁ - ተርጓሚው )

20 Actually, Barara – or Bararah as it is spelled in this source – is only once mentioned in the *Futuh al-Habasha*. However, another royal village which features quite often in the chronicle, Berarah, is likely to be identical with Bararah/Barara (M.-L. DERAT, 2003: 48).

፳፩ ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( በ፳፻፫፤ ገጽ ፻፷፭ - ፻፷፯ ) P.L. STENHOUSE (2003: 165-167).

የእስልምና ተከታዮቹ መካከል፤ ከትልቅ እስከ ትንሹ ድረስ በለጸጉ፤ እናም ከዚያ ወዲያ ረሃብ ከነሱ ዘንድ ጠፋ።

ትንሽ ቆየት ብሎ፤ የአፋሩን ጦር፤ ቀደም ሲል በዞርሲ ኢትዮጵያዊያን ካህናት አስረጂዎቹ ከተገለጠው የርዕሰ-ባላባቱ ቤተክርስትያን እግር ጣለውና ድራሹን አጠፋው። አረብ ፋቂሂ፤ "የርዕሰ-ባላባቱን ግዙፍ የሆነ ቤተክርስትያን አመድ አደረጉት ( . . . )። እስልማን ተካታዮቹ ከቤተክርስትያኑ ሲደርሱ፤ በዚያ የነበረውን ወርቅ፣ ብርን እና የሐር ጨርቅ ወሰዱና ቤተክርስትያኑን አመድ አገቡት።" [፳፪] ከላይ የተገለጡት ክስተቶች ከሞላ ጎደል በርግጠኛነት የበረራን የነገሥታት ዋና ከተማነት ፍጻሜ አወጀ።

አካባቢው በአጼ ልብነ ድንግል ወይንም ተክትለው በወራሾቻቸው እንደገና አልተማረከምና፤ ከዚያ ተከትሎ፤ ከሞላ ጎደል ኦሮሞዎቹ በቋሚነት ሰፈሩበት። ከዚያ በኋላ፤ የኢትዮጵያዊያን የነገሥታት ዋና ከተማዎች ወደ ስሜንና ምዕራብ ራቅ ባለ ቦታ ሆኑ። የበረራ የቀድሞ ሕልውናም ባመዛኙ የተረሳ ሆነ።

ሌላው የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን በዱከም ወንዝ አካባቢ የነገሥታት መቀመጫ የነበረው ባደቀ ነበር። ይህ የሰፈራ ቦታ፤ አረብ ፋቂህ፤ ከአዋሽ ወንዝ የሁለት ቀን የግር መንገድ ነው፤ ይለዋል። በሃንቲንግተን እሳቤ፤ ቦታው ከዛሬዋ ሽኖ፤ የ፳ ማይል የደቡብ ደቡባዊ ምዕራብ አቅጣጫ ርቀት ላይ ነው። [፳፫] ሌላው መላ ምት፤ የባደቀን መቀመጫ፤ ከየረር ተራራ በስተምስራቅ ፳ ማይሎች ራቅ ካለችው ቱሉ ዲምቱ፤ ከተራራ ላይ ያለች አነስተኛ የገጠር ሰፈር፤ ላይ ያደርጋል። [፳፬]

ባደቀ፤ የ፲፭፻፳፱ ዓ. ም. የተካሄደው ዝነኛ ጦርነት የተደረገበት ቦታም ነው። ይህ እንግዲህ፤ የክርስትያንኖቹን ጦር ለከፍተኛ ችግር ከዳረገው ወሳኙ የሽምብራ ኩሬ ጦርነት፤ ከአንድ ዓመት በፊት ነው። የባደቀው ጦርነት፤ የአፋሩ ጦር በክርስትያኖች ጦር ከተቸነፈባቸው አንዱ የመጨረሻው ግጥሚያ ነው። ፉቱህ አል ሃበሽ፤ በከተማዋና በወራሪ የእስልም ተከታዮች መካከል በሚገኝ፤ ሳማርማ "ታላቅ ወንዝ" በተባለው ወንዝ፤ ዳርቻ የተደረገውን ጦርነት በዝርዝር ተንትኖ ይገልጠዋል። [፳፭] ባደቀ፤ እንደ አካባቢው ብዙዎች ሌሎች ታሪካዊ የሰፈራ ቦታዎች፤ በአሕመድ ግራኝ ጦር፤ ተዘርፎ መቀመጫቸው ሆኗል። እናም ይህ፤ በፉቱህ አል ሃበሽ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል።

ጽሑፉ ባደቀን ደጋግሞ "የንጉሡ መንደር" [፳፮] እያለ አጣቅሷል። የአፄ ልብነ ድንግል መቀመጫና ቤተክርስቲያን ባንድ ላይ ያሉባት ቦታ በማለትም ይገልጣል። [፳፯] ቤተክርስትያኑ የተለየ ፍላጎት እንዲኖረው

---

፳፪ ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፻፷፯ ) P.L. STENHOUSE (2003: 167).

፳፫ ጂ. ዳብልዩ. ቢ. ሃንቲንግፎርድ ( ፲፱፻፹፱፤ ገጽ ፺ - ፻፳፫ ) G.W.B.HUNTINGFORD (1989: 90-123).

፳፬ ኤል. ሪቺ (፲፱፻፸፮፤ ገጽ ፻፺፮ ) ደራሲዎቹ ቦታዎቹን ለመለየት/ለመጎብኘት እና ይሄን መላ ምት ለማረጋገጥ፤ ገና ዕድሉ አልገጠማቸውም። ቢሆንም፤ ከየረር ተራራ ራቅ ባሉት በነህ ቦታዎች ላይ የሚቀጣጠል እሳት፤ ዱከም ለሰፈረው የግራኝ ጦር በርግጠኝነት አይታይም። ( ተከታዩን የግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ ) L. RICCI (1976: 196).

፳፭ ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ (፳፻፫፤ ገጽ ፷ - ፷፬ ) P.L. STENHOUSE (2003: 60-64). የሳማርማ ወንዝ የት ላይ እንደሆነ ግልጥ አይደለም። ጂ. ደብልዩ. ቢ. ሃንቲንግፎርድ ( ፲፱፻፹፱፤ ገጽ ፺ - ፻፳፬ ) G.W.B HUNTINGFORD (1989: 90, 124) በግድምድሞሽ፤ የአዋሽ ሰሜናዊ ገባር ወንዝ ብሎ ገምቷል። ሌላ የባደቀን ስፍራ የሚጠቁም በፒ. ኤል. ስቴንሃውስ (፳፻፫፤ ገጽ ፻፷፪ ) "የእስልምና ተከታዮች ዱከም ወንዝ ሲደርሱ፤ ባደቀ መካከል ላይ ጢስ ሲጎን ዓዩ።" በማለት አስቀምጧል። የፉቱህ አል ሃበሽ ዱከም ከየረር ተራራ ተነስቶ ዝቋላ ተራራ አጠገብ ወደ ደቡብ ሄዶ አዋሽ የሚደርሰው ዱከም ጋር አንድ ከሆነ፤ ባደቀ ከየረር ተራራ ደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ወይንም ደቡብ ምዕራብ መገኘት አለበት። አለበለዚያ ከዱከም ሆኖ ሊታይ አይችልም።

፳፮ ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፻፷፪ - ፻፷፫፣ ፻፷፰ ) P.L. STENHOUSE (2003: 162-163, 168)

፳፯ ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፵፰ - ፵፱ ) P.L. STENHOUSE (2003: 48-49). እንደ ፉቱህ አል ሃበሽ፤ በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ሩብ ላይ፤ ባደቀ ለንጉሡ፤ ከሁሉም ከተሞች የበለጠ ዋና ከተማ ነበረች። በዚያን ወቅት፤ ባረራ ቀደም ብላ፤ በ፲ ፫ኛው ክፍለ ዘመን የተነገረላትን በዋናነት የማገልገሉን ቦታ ያጣች ይመስላል።

“እጅግ በጣም በተዋበ ስሌት” በአፄ ልብነ ድንግል ባለቤት፣ በንግሥት ሰብለ ወንጌል የታነፀ መሆኑ፤ ልዩ ትኩረት እንዲሠጠው አድርጎታል። [፷፰] የቤተክርስትያኑን አወዳደም ሲገልጥ፤ የግራኝ የግል ዋና ዘጋቢ፤ ጦረኞቹ ባደቀ ሲደርሱ፤ ኢማሙ “ቤተክርስትያኑን አቃጥሉ!” ብለው ለሰዎቻቸው ትዕዛዝ ሠጡ። እናም ሰዎቻቸው “ባደቀ እንደገቡ፤ ቤተክርስትያኑን አጋዩት። ያጌጡ ምስሎችና ቅርፃ ቀፆች ከወርቅ የተሠሩ ነበሩ። ከላይ ያለው መስቀል ደግሞ ከቀይ ወርቅ የተሠራ ነበር። ወርቁን ገፈው መስቀሉን አቃጠሉና መንደርተኛው ክርስትያን ሲሸሹ፤ ከእንጨት በተሠሩ ምሽጎች የቀበሩትን ተጨማሪ የቤተክርስትያን ንብረት ዘረፉ። ከቤተክርስትያኑ ከዘረፉት ውጪ ሌላ ወርቅ አላገኙም። [፷፱]

ይህ በንዲህ እንዳለ፤ ከፊሉ የእስልምና ተከታዮች ጦር፤ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሌላ የሰፈራ ጣቢያ ነጎዱ። አንዱትና በመባል የተጠቀሰው - ምናልባት እንጦጦን [፸] ሊገልጥ የተጠቀመበት - በአረብ ፋቂህ፤ “በአምበሶች፣ በሰዎች፣ በአዕዋፋት ምስሎች፤ በቀይ፣ በብጫ፣ በአረንጓዴና በነጭ ቀለማትና በሌሎች ቀለማት” ያማረና የተሸቆጠቆጠ፤ የአፄ ልብነ ድንግል “ቤት”፤ ለነገሩ - ቤተ መንግሥት፤ የነበረበት ቦታ ነው። “የእስልምና ተከታዮቹ” ሲነገረን፤ “ወደ ቤቱ ገቡ፤ በውስጡ በነበረው ተደነቁ፣ ከዚያም አቃጠሉት”። ወዲያው ግራኝ፤ አብዛኛው የባደቀ ንብረት ለጥንቃቄ ሲባል፤ ወደሌላ ቦታ ተወስዶ የተቀመጠ መሆኑን ተረዱ። እሳቸውም፤ ከተከታዮቻቸው አንዱን፤ ዋዚር “አዶሊን፣ መልሰው ወደ ቦታው ላኩ። እኒህም ሂደው ለስድስት ቀን ሲዘርፍ ስንብቶ፤ ለኢማሙ፤ “የወርቅና የብር ሳህኖች፣ እና የሐር ጨርቆችን በየዓይነቱ” [፸፩] ይዘውላቸው መጡ። ባደቀ፤ ልክ እንደ በረራ፤ እንደሚታወቀው በክርስትያኖቹ ጦር ተመልሳ አልተያዘችም። ምናልባትም ወዲያው በኦሮሞዎቹ መኖሪያ ሆና፤ ከዚያ በኋላ ከገጽታ ተሰውራለች።

ሌላው በፍራ ማውሮ የ፲ ፬ ፻ ፷ ካርታ የተመለከተው የሰፈራ ቦታ፤ ማሶን ነው። ይህ ቦታ፤ ምናልባት በፋቱህ አል ሃበሽ ከተጠቀሰው ማሲን ጋር አንድ ይሆናል። ጽሑፉ፤ እንዴት የእስልምና ተከታይ ጦረኞች፤ ሞጆ ወንዝ አድረው፤ በበነጋታው ከሰፈሩ እንደደረሱና፤ ሰፈሩን እና የንጉሡን ቤተክርስትያንም እንዳቃጠሉት ይነግረናል። [፸፪]

---

[፷፰] ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፸፩ ) P.L. STENHOUSE (2003: 71).

[፷፱] ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፻፷፫ ) P.L. STENHOUSE (2003: 163).

[፸] ዳግማዊ ሚኒሊክ፤ ከዛሬዋ አዲስ አበባ ቅርብ ቦታ፤ የመጀመሪያውን የንጉሠ ነገሥት ዋና ከተማ ሲመሠርቱ፤ የአጼ ልብነ ድንግልና ዕውቅ ስፍራ በልባቸው ይዘው ነበር። ሆኖም ግን፤ በአፄ ልብነ ድንግል ወቅት የተገኙ ታሪካዊ ምንጮች፤ እንጦጦን አይጠቅሱም፤ ያን የመሰለን ቦታ ደግሞ ወደኋላ የመመለሻ ሐረጉን ለመነተት አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ግን፤ አንቶይኒ ዲ’አባዲ (፲፰፻፺፤ ገጽ ፪፻፺፯ ) Antoine D’ABBADIE (1890: 297), የአካባቢውን መልክዐ ምድር ጥናት ሲያደርግ በነበረበት በ፲፰፻፴ ዎቹ ወቅት፤ በወጫጭ የተራራ ሰንሰለት፤ ከዛሬዋ አዲስ አበባ ምዕራብ “እንጦጦ”ን በትክክል አስቀምጧል። የዳግማዊ ሚኒሊክ የመጀመሪያው እንጦጦ ሰፈር፤ ከዚህ (ወጫጭ የተራራ ሰንሰለት) ደቡባዊ ቁልቁለት ላይ ነበር የተተከለው። ዳግማዊ ሚኒሊክ ዋና ከተማቸውን፤ ከዛሬዋ አዲስ አበባ ሰሜን፤ ወደ ገዘፈው የተራራ ሰንሰለት ባሻገሩበት ወቅት፤ ይህ ስያሜ፤ ከዚያ ጊዜ ወዲህ በሚታወቅበት፤ እንጦጦ የሚለው ስም፤ የተከተለው ይመስላል። ሆኖም ግን፤ ከአዲስ አበባ ሰሜን የሚገኘው የዚህ ተራራ ሰንሰለት አርኪዮሎጂካል መረጃ፤ እንቆቅልሽ ነው። በራጉዔል ቤተ ክርስትያን ዙሪያ የተገኙ፤ የአንድ ምሽግና የሌሎች ሕንፃዎችና የምሽግ ውቅሮች፤ ከተገኘው ፍርስራሽ ውስጥ፤ ምናልባት አመዝኖ የሚገኘው ከሞላ ጎደል በዳግማዊ ሚኒሊክ ዘመን የተገነባ ነው የሚያስብ ሆኖ፤ የተራራውን ጫፍ የከበበው ምሽግ ደግሞ፤ ከዚያ እጅግ በጣም ቀደም ብሎ የተሠራ ይሆናል። ይህ ዕጣ ደግሞ፤ ከማርያም ቤተክርስትያን ሰሜን፤ ከፍ ባለ ቦታ አጓጉል በሆነ መንገድ የተጠበቀው የግድግዳ ፍርስራሽ ይመስላል።

[፸፩] ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፻፹፯ ) P.L. STENHOUSE (2003: 187).

[፸፪] ፒ. ኤል. ስቴንሃውስ ( ፳፻፫፤ ገጽ ፷ ) P.L. STENHOUSE (2003: 60).

“የእስልምና ተከታዮች ጦርም ጉዞውን ጀመረ። በፈጣገር ምድር፤ ሞጁ ከሚባል ወንዝ ሲደርሱ፤ ለከሰዓት በኋላ ጸሎታቸው አረፉ። በዚች ቀን፤ ቀዝቃዛና የሚጋፋ ነፋስ ነበረና፤ ሌቱን እዚያው አሳለፉ። ሲነጋ፤ ጉዟቸውን ተያያዙትና ማሲን የሚባል፤ የኡመር አቡን ቦታ ሲደርሱ አቆሙ። ያን እሳት ለኮሱት፣ የንጉሡንም ቤተክርስትያን አጋዩት። ( . . . ) በሶስተኛው ቀን ተነሱና በመጨረሻም ባደቀ አጠገብ ደረሱ። ይህ የንጉሡ ቤቶችና የሱ ንብረት የተቀመጠበት ነበር።

ይህ ገለጻ፤ በፍራ ማውሮ ካርታ ከተመለከተው የማሶን ቦታ ጋር በደንብ ያገጣጥመዋል። አክሎም፤ ባደቀ፤ ከማሲን/ማሶን ከአንድ ቀን ያነሰ የጉዞ ርቀት ላይ መሆኑን ያመለክታል።

## የመልክዐ ምድር ሁኔታና የመካከለኛው ዘመን የመጓጓዣ መንገዶች ስርዓት

በደቡብ ሸዋ የመካከለኛው ዘመን የሰፈራ ቦታዎች ስንመረምር፤ የአካባቢው መልክዐ ምድርን እና ሊኖሩ የሚችሉትን የመካከለኛው ዘመን የመጓጓዣ መንገዶች ስርዓት በግንዛቤ መወሰድ አለባቸው።

የሚከተለው ምስል፤ ከየረር ተራራና ከዱከም ወንዝ በስተምዕራብ በኩል ያለው አካባቢ፤ ከሞላ ጎደል ምንም ወንዝ ያማያግደው፤ ሰሜን ምሥራቅ አካባቢን ከደቡብ ምዕራብ አካባቢ፤ እንዲሁም ከሰሜን ምዕራብ እና በደቡብ ምሥራቅ ካለው የስምጥ ሸለቆ ጋር ማገናኛ የሰላ የመንገዶች ቅንብር፤ ስልታዊ ቦታነቱን ያሳያል። በባህል የተለመደው የመጓጓዣ አኳኋን ( በበቅሎ፣ በአህያ፣ ወዘተ.) በጥቅሉ ጥሩ እንቅስቃሴ ቢኖረውም፤ የመካከለኛው ዘመን የመገናኛ መስመሮች አጣጣል፤ የሚያቋርጧቸውን ወንዞች ቁጥር በማሳነስ ላይ የተመሠረተ ነበር፤ ብለን እናምናለን። የዝናቡ ወራት እንዳለፈ፤ በተቻለ ፍጥነት ማሻገር የሚችሉ፤ ቀለል ያለ መሻገሪያ ያለባቸው ቦታዎች ተምርጠው ነበር። በዚህ በኩል ሲታይ፤ የክርስትያኖች ንጉሥ ነገሥት ግዛትን ከጅማ/ከፋ - ደብረ ብርሃን - ቀይ ባህር ያለውን የንግድ መስመር ለማገናኘት፤ በየረር ተራራ አካባቢ ያለው ቦታ፤ አመቺ ሆኖ ተቀምጦ ነበር። በሰሜን በኩል ያለውን፤ ዛሬ እንጦጦ ተብሎ የሚታወቀውን ግዙፍ የተራራ ሰንሰለት በማቋረጥ፤ በአባይ ሸለቆ ካሉት የሰሜኑ ክፍሎች ጋርም በትክክል፣ በቀጥታ ተገናኝቷል። ለክርስትያኑ ንጉሥ ነገሥት ግዛት፤ ይህ ሁሉ ለደቡብ ሸዋ ዋናነት አስተዋጽዖ አድርጓል። ( **ስዕል ፫ን ይመለከቱ** )

በአካባቢው እስካሁን የታወቁ የአርኪዮሎጂ ቦታዎች ብዛት፤ የቦታውን ዋናነት የሚያረጋግጥልን ይመስላል። የመካከለኛው ዘመን መናገሻ ተራራ (ዙፋን የሚጭኑበት) እና በሰሜን ምዕራብ የወጨጫ ሰንሰለት ተራራ ( እንጦጦ?) ብዙ ፍርስራሾች ያሳያሉ፤ ምናልባት ከ፲፫ኛው እስከ ፲፮ኛው ክፍል ዘመን ነገሥታቱ በደቡብ ሸዋ ያሳነጿቸው ተዛማጅ ቤተክርስትያናት፤ ( እንስላሌ፣ ግንቢ፣ ጉጂ ኪዳነ ምህረት፣ ጉቱ፣ ኢላላ፣ ጋዳ፣ ኤጀርሳ፣ **ስዕል ፫ን ይመለከቱ** ) እና ከሁሉም የጎላ ደግሞ፤ በደቡብ በኩል የመካከለኛው ዘመኑ፤ ዝቋላ ተራራ ላይ ያለው ገዳም። ከዝቋላ ተራራ በስተቀር፤ ሁሉም የተጠቀሱት ቦታዎች፤ በደጋማው ከፍታና በቆላማው ዝቅታ መካከል ባለው ደንበር ቦታ፤ ያም ከባህር በላይ ፳፻ እና ከባህር በላይ ፳፻፭፻ ከፍታ ላይ፤ ማለትም የወይና ደጋ ዓየር ጠባይ ባለው፤ ልክ በዞርሲ የጉዞ ዘገባ፤ የበረራ አየር ጠባይ እንደተገለጠው፤ የተቀመጡ ናቸው።

---

፴፫ የቀድሞ የሰፈራ ቦታዎች አስተናነፅ፤ ግራኝ ከማፍረሱ በፊት ከነበሩ ቤተክርስትያናት ጋር፤ ሲያዩት እጅግ ተመሳሳይ የሆነ የአራት ማዕዘን ሕንፃ ፍርስራሽ፣ በመናገሻ ተራራ ላይ በተጨማሪም መጠነ ብዙ የሆነ ጥበብ የተሞላበት የሸክላ ዕቃዎች፣ ሌላም በቁፈራ የተገኙ ፍርስራሽ የቀድሞ ሰዎች ዕቃዎች፤ ይህን ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ የሚገኝ የታወቀ የመሬት ከፍታ ዋናነት ያረጋግጣል። ( ኤፍ. አንፍሬይ፣ ፲፱፻፸፰፣ ገጽ ፻፶፱ን የመልከቱ) (see F. Anfray, 1978: 159).

## ጥናት የተካሄደበት አካባቢና የተወሰዱ ግምቶች

ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ፤ በወጨጫ የተራራ ሰንሰለትና በአቃቂ ወንዝ መካከል በስተምዕራብ፣ የየረር ተራራ በስተሰሜን፣ የዝቋላ ተራራና የአዋሽ ወንዝ በስተደቡብ፣ እና የሞጆ ወንዝና ደብረ ዘይት በስተምሥራቅ ሲሆን፤ የ፺ ኪሎ ሜትር የታቀፈ መሬት (ስኩዌር) ነው። የተደረገው ጥናት፤ በሚከተሉት ግምቶች የተመሠረተ ነው።

- የመካከለኛው ዘመን የሰፈራ ቦታዎች፤ አመቺ በሆነ የስልት ቦታ ላይ መቀመጥ አለባቸው። ይህም ማለት፤ ከሌሎች ዋና ዋና ቦታዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ያለው።
- የነገሥታት "ከተሞች"፤ በተራራ ጫፍ ላይ ወይንም ቢያንስ የጎላ ከፍታ ካለው ቦታ ላይ መቀመጥ አለባቸው።
- የነገሥታት የሰፈራ ቦታዎች፤ ለማስረጃ የሚሆን፤ በግድግዳዎች መልክ፣ ጉድቦች፣ እና ሌሎች የእነፃ ሥራዎችን የሚያመላክት፤ የተወሰነ ብዛት ያለው የሸክላ ሥራ፣ ሰው ሠራሽ መገልገያ መሣሪያ፣ አጥንት፣ ወፍጮና ሌሎች ሰዎች ለአስርታት ዓመታት የኖሩበት ቅሪቶችን፤ ሊሠጡ ይገባል።

### የጥናቱ ዘዴና የመስክ ጉብኝቶች

በ፺ ኪሎሜት ዝርግ መሬት (ስኩዌር) ቦታ ውስጥ የሚደረግን የመስክ ጥናት ለማካሄድ፤ የተዳቀለ ዘዴ ተመረጠ፤ (ሀ) ቦታው - በተለይ ደግሞ ጉብታዎችና ከፍተኛ ቦታዎች - የጉግል መሬት የሳተላይት ምስል ቀራጩን ተጠቀምን፤ እና (ለ) የመስክ ጥናት ጉዞዎች፤ የሰፈራ ሕንፃ መኖራቸውን የሚያመላክት የሚመስሉ ቦታዎች ላይ ተደርገዋል። የምስሉ ጥራት፤ በአብዛኛው ጥናቱ በተደረገበት ቦታ በበቂ ትክክለኛ እና ዝርዝሩም የተለየ ትኩረት ለመሥጠት፤ "ቅድመ-መረጣ" ለማድረግ የሚያስችል ነው። ቢኖንም ግን፤ ከየረር ተራራ ምሥራቅና ሰሜን የምስሉ ጥራት ዝቅተኛ ነው፤ የግድም በአካል በቦታው ተገኝቶ፤ የመስክ ጥናት ማድረጉ አማራጭ የሌለው ሆነ። በተጨማሪም፤ የሳተላይቱን ምስል በትክክል መተርጎሙ፤ የተወሰነ ልምድ ይጠይቃል። በስህተት መተርጎሙ፣ ካንድ ጊዜ በላይ፤ የ "ጥንት" ግድግዳዎችን "ግኝት" አስከትሎ፤ ቦታው ሲጎበኝ፤ የተፈጥሮ ጉዳይ ሆኗል። ጉብታዎችና ተራሮች፤ በተለይም መንስዔያቸው እሳተ ጎመራ የሆነ፤ በተደጋጋሚ ሰው ሠራሽ የግንብ ፍርስራሽ ምስልን ያንፀባርቃሉ። በዚህም አለ በዚያ፤ የሳተላይት ምስል፤ የመቋደሻ ዕይታን ብቻ ይሠጣል፤ ተለይተው፣ "የተጠረጠሩ" ቦታዎችን በአካል ሄዶ በመጎብኘት ማረጋገጡ፤ ምንጊዜም አስፈላጊ ነው። ቦታውን በዓይን መቃኘቱ፤ ከተቻለ ካካባቢው ከፍተኛው ጉብታ አናት ላይ በመሆን፤ ያለምንም ጥርጥር የግድ አስፈላጊ ነው። ጥናቱ በተካሄደበት ቦታ ክፍሎች በሙሉ፤ ተደጋጋሚ የመስክ ጉብኝቶች ተካሂደዋል። የሚከተሉት ቦታዎች ተጠንተዋል፤

- የአቃቂ ወንዝ ምዕራባዊ ክፍል፤ የወጨጫ ተራራማ ሰንሰለት እና አካባቢ ጉብታዎቹና ቁልቁለቶቹ፣ የመናገሻ "ዙፋን መጫኛ" ጉብታን ጨምሮ፣ ፉሪ ተራራና ከፉሪ ተራራ ደቡብ እና ከአባ ሳሙዔል ሐይቅ ምዕራብ ያሉ ዝቅተኛ ጉብታዎች
- በአቃቂ ወንዝና ከዱከም ወንዝ መካከል፤ ቆየ፣ ኮራ፣ ጋራ ቡሹ፣ እንስላሴ ጢቆ ጉብታዎችና፣ ጉጂና ቢልቢሎ ተራራ
- ከዱከም ወንዝ ምሥራቅና ከሞጆ ወንዝ ምዕራብ እና ከሞጆ ወንዝ ምዕራብ፤ የዝቋላ ተራራና ከደብረ ዘይት ተነስቶ እስከ ዝቋላ ተራራ ድረስ ያሉት የእሳተ ጎመራ ፎብታዎች

(ከደብረዘይት ደቡብ በሚገኘው የበደ ገባቤ ቦታ ያለውን ግዙፍ የእሳተ ጎመራ ክፍት ቅሪት ጨምሮ)፣ የየረር ተራራ - በተለይም ወደ ዱከም የሚወስዱ የጉብታ ሰንሰለቶች (ጨፌ ቡኪ፣ ኑኞ፣ ጊማሸ፣ ተዴቻ) - እናም የየረር ተራራ ምሥራቃዊ ቁልቁለት (ጋላ አምባ፣ ከተባ፣ ወደቻ፣ ሲሬ፣ ኢቼቼ)፣ በየረር ተራራና በደብረዘይት መካከል የሚገኘው የሃዳ ዝርግ መሬት

- ከሞጆ ወንዝ ምሥራቅ፤ የሮብ ( ቀኑን ረቡዕን የሚዘክረው ) ገበያ መንደርና ያካባቢው ጉብታዎች (ሂዲ፣ በሮራ፣ [፴፬] ወፉ)

ከየረር ተራራ ሰሜን እና በስተምሥራቅ ደግሞ ራቅ ብሎ የሚገኘው ቦታ፤ በጥራቱ ማነስ የተነሳ፤ የሳተላይት ምስሎችን በመጠቀም፣ በትኩረት ጥናቱ ሊካሄድበትና በጥንቃቄ ሊፈተሽ አልተቻለም። እነህ አካባቢዎች፤ አሁንም በቦታው ተገኝቶ የመስክ ጥናት ሊደረግባቸው ይገባል። እኒህ ከጥናቱ ዕቅድ አካባቢ ውጪ ናቸው። [፴፭] ከአቃቂና አባ ሳሙዔል ሐይቅ ምዕራብ የሚገኘውም አካባቢም፤ በጥናቱ ሂደት አልፎ አልፎ ብቻ ተጎብኝቷል፤ የጉግል ኧርዝን ምስል በመጠቀም አካባቢው ቅድመ ፍተሻ ቢያንስ ሊደረግበት ይቻላልና፤ እንዲሁ በቦታው ተገኝቶ የመስክ ጥናት ሊደረግበት ይገባል።

## የጥናቱ ውጤቶች

ጥናቱ ሶስት፤ ቀደምትነት ያላቸው ቦታዎችን ለይቶ አውጥቷል። እኒህ ፍጹም የተለያዩ ቦታዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### (ሀ) የወጨጫ ተራራ ሰንሰለት ምሽጋ፤

ምሽጉ የተገኘው በወጨጫ ተራራ ሰንሰለት ደቡብ ምሥራቃዊ በኩል ነው። ከባሕር ወለል በላይ ፫፪፻ ሜትር ከፍታ ላይ፤ ባንድ የሩቅ ጉብታ ላይ ፪ ኪሎ ሜትር ከዳሞጫ ተራራ ( ከባሕር ወለል በላይ ፫፫፻፹፯ ሜትር ከፍታ ላይ አናቱ ላይ ያለ) ርቀት ባካባቢው ላይ ጎልቶ ተዘርፍጧል። በላቀ ከፍታው ምክንያት፤ ልዩ የሆነው ጉብታ፤ ከምሽጉ ጋር፤ ከሰማዩ ጋር ሲታይ ከሌላው ሁሉ ጎልቶ በመውጣቱ፤ ከምዕራብ በኩል ካልሆነ በስተቀር፤ ከሁሉም አቅጣጫ ይታያል። [፴፮] **(ስዕል ፬ን ይመልከቱ)**

በሩቅ ካለው ዘዋራ ጉብታ አናት ላይ ያለው ምሽግ፤ የወጨጫን እሳተ ጎመራ ክብ ሰምጥ ከሠራው አንዱ ጉብታ ላይ ውሏል። ከባሕር ወለል በላይ ፫፪፻ ሜትር ከፍታ ላይ ውሎው፤ ጉብታው፤ በሰሜን፣ በምሥራቅና በደቡብ በኩል፤ ጭልጥ ባለ አዘቅት ወይም ቁልቁለት፣ ይሄ ቀረሽ የማይባል ጥበቃ አለው። በምዕራብ በኩል ብቻ፤ ጠባብ የኮረብታ ትከሻ ጉብታውን ከአጓደኙ ጉብታዎች ጋር ያገናኙታል። (**ፎቶ ፩** )

---

፴፬ በሮራ፤ ከሮብ ገበያ መንደር ደቡብ፤ ከደብረዘይት በስተምሥራቅ በጥቂቱ ፲ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ የሚገኝ ቦታ ስም ነው። ምናልባት ክራውፎርድ በረራን ከቦሮራ፤ ከእንግሊዞች የጦር ካርታ ላይ ያገኘውን፤ ከአዲስ አበባ ደቡባዊ ምሥራቅ፣ ለደብረዘይት ቀረብ ያለ ተራራ ያገኘው፤ ጋር አመሳስሎ ባሳቡ የያዘበት፤ በሮራ ተብሎ የሚጠራ ትንሽ ኮረብታም አለ። ቢሆንም ግን፤ ይህ ጥናት፤ በአሁኗ በሮራ፤ የመካከለኛው ዘመን ከተማ ምንም ዓይነት ቅሬት አላገኘም።

፴፭ በየረር ተራራ ሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ የሚገኘው ቦታ፥ ለመካከለኛው ዘመን ከተማ ዝርግና መሸጎ ለመከላከል የማይመች ነው፤ ሆኖም ግን፤ በረራ ምሽግ ነበረባት ወይንስ አልነበረባትም የሚለውን ማረጋገጫ ስለሌለ፤ ይሄ ግምት ስህተት ሊሆን ይችላል።

፴፮ የመልክዐ ምድር አቀማመጥ Geographical position: 8o 58’30”N, 38o 36’56”E.

የጉብታው አናት፤ ፳፯ ሄክታር ( አንድ ሄክታር ፻ በ ፻ ሜትር የሆነ የታቀፈ ስፍራ ነው ) ግዙፍ ዝርግ ቦታ፤ ዙሪያ ገጠሙን ጫና ያለው የ ፩ ነጥብ ፯ ኪሎ ሜትር ርቀት፣ ከ ፫ እስከ ፭ ሜትር ድረስ ወርድና ከግማሽ እስከ አንድ ተኩል ሜትር ቁመት ያለው የግንብ አጥር አሉት። ይህ የውጪ የግንብ አጥር (ውግ) ተረተሩን ተከትሎ፤ የጉብታውን አናት ስጥ ሜዳ፤ ወደ አዘቅትና ቁልቁለት የሚሄድበትን በመተው፤ የጉብታውን የተፈጥሮ መከላከያነት ተጠቅሞበታል። (**ፎቶ ፪ እስከ ፬** )

ሌሎች ዋና የሚባሉ ገጽታዎቹ፤ ክብ የግምብ አጥር (ክግ)፤ ፷ ሜትር የክቡ መቀነት ርቀት፣ ፪ ሜትር ወርድና ከግማሽ እስከ አንድ ሜትር ቁመት ያለው (**ፎቶ ፫**) የሆነ፣ ከፊል የግምብ አጥር (ከግ)፤ ፯፻ ሜትር ርቀት፣ ከ ፫ እስከ ፭ ሜትር ወርድና አንዳንድ ክፍሉ እስከ ፩ ነጥብ ፯ ሜትር የሚደርስ ቁመት ያለው (**ፎቶ ፮**) ናቸው። የክብ ግምብና የከፊል ግምብ አጥሮቹ፤ ብቸኛ በሆነው የምሽጉ መግቢያ በር (መ) ቅርብ ነው የተቀመጡት። የምሽጉ በር፤ በምሽጉ ምዕራባዊ ወገን፤ ጉብታውን ከቀሪው የወጨጫ ስንሰለታማ ተራራ ጋር ወደሚያገናኘው ዝርግ ተረተር ላይ ነው። ከምሽጉ በር በተጻራሪ ወገኑ፤ ከሞላ ጎደል አራት ማዕዘን ያለው፤ የተጠናከረ ሾጣጣ፤ የግምብ አጥር አለ። ይሄ በግምት ከሁሉም የቦታው ጎኖች የጎላ ደካማ ጎኑ ያለበትን ለመጠበቅ ይሆናል። ከተጠናከረው ሾጣጣ ግምብ አጥር ጎን ያለ አንድ ምንጭ (ም)፤ የነዋሪዎችን የወሃ ፍላጎት በቂ አይደለም። እናም የጎደለውን ለመሙላት፤ ከምሽጉ በታች ካለው ወንዝ በመውረድ ብቻ ይሆናል (**ፎቶ ፪ እስከ ፫** )።

የጉብታው አናት፤ ሌጣ አለት ደንጋይ ያለበት አካባቢን ይጨምራል። ቢሆንም፤ አሁን፤ አብላጫውን ፳፯ ሄክታር በግምብ የታጠረ ቦታ፣ ሰዎች ይጠቀሙበታል። አሁንም ከሚያስደንቁት የግምብ አጥሮቹ ውጪ፤ ምንም ዓይነት ከደንጋይ የተሠራ  ምንም ዓይነት ከደንጋይ የተሠራ የዕነፃ ሥራ፤ ለምሳሌ እንደ የሕንፃዎች ፍርስራሽ ያለ፤ ተለይቶ ሊታወቅ አልተቻለም። እኒህ ከነበሩ፤ አንጻራዊ ብርቱነት ያለው የአካባቢው የእርሻ ክንውን፤ መረጃውን አጥፍቶት ይሆናል። ከፊል የግምብ አጥሩ አካላት፤ ደንጋዮቹ በርግጥ በደንብ በመተከላቸውና አንዳንድ እደሳም ተጨምሮላቸው፤ አሁንም እስከ ፩ ነጥብ ፯ ሜትር ከፍታ ድረስ ቆመዋል ( በተለይ ከከፊል ግምቡ )። ደንጋዮቹን ለመጠገን፤ ሎሚ የተጠቀሙ ይመስላል። ሆኖም ግን፤ አብዛኛው የግምብ አጥሩ ቅንብር፤ አጉል የተሸረሸረ ግምብ ሆኖ፤ ያም ወደ ፍርስራሽነት ተቀይሯል። የውጪው የግምብ አጥር፤ የመነሻ ፭ ሜትር አስደናቂ ወርድ ኖሮት፤ አሁን ግን አንዳንድ አካሉ ተሸርሽሮ በመሬቱ ወለል ተዘርግፏል (**ፎቶ ፬** )። ቦታው፤ ሰዋች ጠርቀም ብለው ከሰፈሩባቸው መኖሪያዎች ሩቅና ዘዋራ መሆኑን ከግምት በማስገባት፤ ከግምብ አጥሩ ደንጋይ ወይንም ከሕንፃዎቹ ወስዶ ለሌላ አገልግሎት ማዋል መቻሉ፤ በጣም ዝቅተኛ ዕድል ያለው ይመስላል።

ምሽጉ ካለበት ጉብታ ሥር ያሉ ነዋሪዎች፤ ስለ ግምብ አጥሮቹ ያውቃሉ። ስለ አመሠረታቸውም የተለያዩ ግንዛቤዎችና ገለጻዎች አሏቸው። ከነኝህ አንዱ፤ ይህ፤ እንደተዘገበው፤ በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት ምዕራባዊ ቁልቁለት በኩል የሚገኘውን የመናገሻ ጫካ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲጠበቅ ያደረገው ገዥ፤ የ ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ንጉሠ ነገሥት፤ የንጉሠ ነገሥት ዘረ ያዕቆብ ዋና ከተማ ነበር። [፴፯]

---

፴፯ እውነተኛነታቸው በትክክል ላልተረጋገጠ ከትውልድ ትውልድ በቃል እየተነገረ የወረደው ታሪክ፤ ኤፍ. ቮን ብሪትንባኽ እና ጄ. ኪኮል (፲፱፻፷፪፣ ገጽ ፲፰ ይመልከቱ ) see F. VON BREITENBACH & J. KEUKOL (1962: 18); በተጨማሪም ኢ. ኤፍ. ጊልበርት (፲፱፻፸) and E.F. GILBERT (1970). *ሁለቱም ጽሑፎች፤ ንጉሡን ያዕቆብ ብለው ይጠቅሳሉ (የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመንና የ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አፄ፤ ካካባቢው ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት የሌላቸውን)። በሌላ በኩል፤ የአካባቢው ቄስ፤ ግራጌታ ወርቅነህ፤ የካባቢያችን ባህላዊ ትውስታችን፤ የመካከለኛው ዘመን በአካባቢው የነበረው የሥልጣኔ ዕድገት፤ ዋና ከተማቸው በዚህ አካባቢ፤ ደብረብርሃን፤ የነበረው፤ በጣም ኃይለኛ የነበሩት የ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ንጉሠ ነገሥት ዘረ ያዕቆብ ነው ብለው ለኒህ ለዛሬዎቹ ጸሐፊዎች ነግረዋል። ያዕቆብ የሚለው ከላይ በተገለጡት ጸሐፊዎች የተጠቀሰው፤ ዘረ ያዕቆብን አሳስተው ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም፤ በዚህ አካባቢ፤ በዚያ ዘመን፤ ያዕቆብ የሚል ስም የነበረው ንጉሥ አልነበረም።*

የአካባቢው፤ ከትውልድ ትውልድ በቃል እየተነገረ የወረደው ታሪክ፤ በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት ላይ፤ የዘረ ያዕቆብ የፈረሰ ከተማ እንዳለ፤ ቀደም አድርጎ ያመለከተ ይመስላል። ይሄንኑ መረጃ፤ ዲ’ አባዲ[፴፳] በተራራው ሰንሰለት ላይ፤ አንድ “የዘረ ያዕቆብ የፈረሰ ከተማ” ስላለው ቦታ፤ አንጻራዊ ትክክለኛ የሆነ የመልክዐ ምድር አቀማመጥ ዝርዝር መረጃ ሲያቀርብ፤ ያንጸባርቀዋል። ይህ በሱ የተገለጠ ቦታ፤ እኛ ከተራራው አናት ላይ ካገኘነው ጋር፤ ሙሉ ለሙሉ አንድ ነው።

### (ለ) እንስላሌ ጢቆ፣ ጋራ ቡሹና ኢቺቼ ላይ ያሉ ደልዳላ ቦታዎች የተሠላቸው የጉብታ አናቶች

ከየረር ተራራ በስተምዕራብ ተጠግቶ፤ እንስላሌ ጢቆ በሚባል ቦታ፣ አንድ ጉብታ የተለዩ ገጽታዎችን ያሳያል፤ በእሳተ ጎመራ ያልጠነከረ ነገር የዳበተው መሬት ላይ፤ ሶስት በጉብታው አናት ስጥ ሜዳ ዙሪያ፤ ተቆፍረው የተሠሩ ደልዳላዎች አሉ (ፎቶ ፮ )። ከባህር በላይ ፳፫፻፬፰ ሜትር ከፍታውና አዘቅት ቁልቁለቱ ጋር ያካባቢውን አድማስ፤ ወደ ዱከም ወንዝ [፴፱] የሚያመራውንም ጅረት ጨምሮ ስላጥለቀለቀው፤ እኒህ የጉብታው ገጽታዎች ከሩቅ መታየት ይችላሉ። ደልዳላ ስፍራዎቹ ሰው ሠራሽ መሆናቸው ግልጥ ነው። የእሳተ ጎመራ ውጤት የሆነውን ቀለል ያለ አፈር፥ ሕንፃዎችን ለማቆም የማይመች መሆን በማጤን፤ እኒህ ደልዳላ ስፍራዎች፤ ሰዎች ሆን ብለው ለደንጋይ ፍልፈላ ወይንም ለሌላ ጉዳይ ያከናወኑት ብሎ ለመተርጎም ባመዛኙ አይቻልም (ፎቶ ፮ )።

ግማሽ ሄክታር ብቻ ሆኖ፤ በአንጻራዊ አነስተኛው የጉብታ አናት፤ የተቀመጡ ደንጋዮችና ከፊል የግምብ አጥሮች (ግ)፤ በግልጥ ሰው-ሠራሽ እና ከፊል የምሽግ ቅንብርን የሚያሟሉ ይመስላሉ። ይህ ደግሞ፤ በጉታው አናት ከፍተኛ ቦታ ላይ ለሚገኙት (ፎቶ ፰ )፤ የ፪ እና የ፬ ሜትር የወገብ አጋማሽ ላላቸው ጥንድ የደንጋይ ክቦችም (ደክ) በተመሳሳይ ለመግለጥ ያስኬዳል። በደቡባዊ ምሥራቅ በኩል ያለ ለመከላከያ የተቆፈረ ጉዳባ ቅንብር፤ ለራሱ ለጉብታው አናት መግቢያ (መ) የሚያመለክት ይመስላል። ሆኖም ግን፤ ባጠቃላይ ለቦታው በተደረገው በጣም ዝቅ ያለ የመንከባከብና የጥበቃ ምክንያት፤ ግልጥ የሆኑ አመላካቾች፤ ለምሳሌ እንደ የግምብ አጥሮች ያሉ፤ ጉዳዩን በርግጠኝነት ለማስቀመጥ የሚረዱ አልተገኙም። በጉብታው ሰሜን በኩል የሚገኘው፤ የእሳተ ጎመራው ውጤት በሆነው አፈር ላይ ጥልቀት ያለው ጉድብ፤ ለመከላከያ አገልግሎት የተቆፈረ ይሆናል። በጉብታው አናት ላይ፤ መጠነ-ብዙ የሸክላ ሥራዎች ይገኛሉ። ከኒህ፤ ጥቂቶቹ፤ በአንጻሩ ሲታይ የላቀ፤ ረቂቅ የሸክላ ሥራ ናቸው። በተጨማሪ፤ ካንደኛው የግምብ አጥር ሥር፤ ፳ ሴንቲ ሜትር የሚሆን ጥልቀት ላይ፤ አንድ ሰማያዊ ቀለም ያለው የመስተዋት ስባሪ ተገኝቷል። በዚያ ቦታ ላይ፤ የተፈጥሮው የንጣፍ ወለል፤ ጥቂት የሸክላ ሥራዎችና ከሰል መገኛ ወለልን ይተካዋል። በዱከም ወንዝ ማዶ፤ በየረር ተራራ፤ ቁልቁለቱ ቀለል ያለ መውረጃ ባለው በኩል፤ ከበስተምሥራቁ የተገኘ አንድ አነስተኛ የሰፈራ ቦታ፤ በተሻለ መጠን መንከባከብ የተደረገላቸው ፍርስራሾች፤ በግልጥ በጣም ቀረብ ያለ መነሻ አላቸው።

ከአሁኗ የዱከም ከተማ ሳይርቅ፤ ከእንስላሌ ጢኮ መገኛ ቦታ፤ ደቡብ-ምዕራብ ፮ ነጥብ ፰ ኪሎ ሜትር የሚሆን ብቻ ርቀት ላይ፤ ሌላ የተመሸገ የጉብታ አናት፤ ጋራ ቡሹ[፵] ላይ ተገኝቷል። ከእንስላሌ ጢኮ ፍጹም በተለየ መንገድ፤ በቦታው፤ ሰፊ፤ በግምት ፯ ሄክታር የሚሆን፤ በአምባው ላይ የተዘረጋ መሬት አለ። አምባው፤ ከጫፉ ከ ፳፫፻፵፮ ሜትር ከባሕር በላይ ከፍታ ተነስቶ በዘገምታ ወደ ታች ያቆለቁላል። የቦታውን ማዕከል፤ የግዙፍ ደጋዮች ክብ ( በግምት ፹ ሜትር የወገብ ስፋት ያለው ) አሳፍቶ ይዞታል።

---

፴፳ ኤ. ዲ’አባዲ (፲፰፻፺፥ ፪፻፺፯) A. D’ABBADIE (1890: 297).

፴፱ የመልክዐ ምድር አቀማመጥ፤ 8o 52’48”N; 38o54’02”E; the Dukem ford is on 2.230 m asl.

፵ የመልክዐ ምድር አቀማመጥ፤ Geographical position: 8o 50’56”N; 38o50’48”E.

የግምብ አጥሮችና የግምብ አጥር ክቦች ያሏቸው ሰፋ ያለውን ክፍል የያዙ የተደለደሉ ቦታዎች፤ ምናልባትም ከእንጨት የተሠሩ ጎጆዎች ሰፈር መሆኑን የሚያመለክቱ፤ ወደ ሰሜን ምሥራቁና ሰሜናዊ ክፍሉ ይገኛሉ። ከሞላ ጎደል ለጥ ባለው ዝርግ መሬት ላይ፤ ከነጥብ ሶስት እስከ አንድ ተኩል ሜትር ያለው አንድ ጉድብ ምሰን፤ እስከ የሜትር ሶስት ሩብ ድረስ፤ በዛ ያሉ የሰው ሰፈር ቅሪቶችን፤ ( የሸክላ ሥራዎች፣ ወፍጮ፣ ባልጩት) ውጤት ተገኝቷል። የሰፈሩ አጠቃላይ ንድፉ አሁንም በግልጥ የሚለይ ቢሆንም፤ ሁሉም የግምብ አጥር ቅንብሮች በጣም ተሸራርፈውና አጓጉል ሆነዋል። [፵፩]

ከታች ከተገለጠው ስፍራ ቅርብ የሆነ፤ ከእንስላሌ ጢቆ ከተገኘው ጋር ተመሳሳይ የሆነ፤ የጉብታ አናት ደልዳላ መሬት ገጽታዎች፤ ከየረር ተራራ ምሥራቅ በኩል ተገኝቷል። ይህ የጉብታ አናት፤ ሊቼቼ (**ፎቶ** ፴ ) ተብሎ በሚጠራ ቦታ ይገኛል። ይህ ቦታ፤ ገና በዝርዝር መመርመርና መጠናት አለበት።

### (ሐ) የ “ሲሬ ከተማ” የረር ተራራ ላይ

፲፰ ኪሎ ሜትር የሚሆን ከደብረዘይት ሰሜን፣ ወደ ጨፌ ዶንሳ በሚወስደው ኮረኮንች መንገድ አጋማሽ ላይ፣ የገበያዋ ከተማ ጎዲኖን ፪ ኪሎ ሜትር እንዳለፉ፤ አንድ በጣም አስደናቂ የአርኪዮሎጂ ስፍራ ተገኝቶ ብትንትን ተደርጎ ተጠንሯል። ቦታው ባካባቢው “ሲሬ” ተብሎ ይታወቃል። እናም ደራሲዎቹ የአርኪዮሎጂ መረጃውን ለመጥቀስ፤ ስፍራውን “የሲሬ ከተማ” ብለው ሰይመውታል። ከዚህ ቦታ፤ ወደ ሰሜን-ምዕራብ ፮ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ፤ የመካከለኛው ዘመን የጊምቢ ቤተክርስትያን ፍርስራሾች ይገኛሉ። ወደ ምዕራብ ደግሞ፤ ራቅ ሳይል፤ የየረር ተራራ ያንዣብባል። [፵፪] ወደ ሰሜን-ምሥራቅ ፪ ኪሎ ሜትር ብቻ ራቅ ብሎ፤ የእቼቼ ጉባ አናት ደልዳላ ስፍራ አለ። ( ስዕል ፯ን ይመልከቱ )

ቀድሞውንም ሪቺ፤ በ፲፱፻፸፫፤ ጊንሚ ላይ ቁፈራውን ሊያካሄድ ስፍራውን አንድ ኪሎ ሜትር በሚሆን ርቀት ሲያልፈው፤ በጉታው ላይ ያሉትን የግምብ አጥሮች ያመላከታቸው ይመስላል (**ፎቶ** ፲ )። ጥናቱን ለማካሄድ ጊዜ እንደሌለው ይዘግባል፤ ነገር ግን፤ የዚያን ጊዜው የፈረንሳይና ኢትዮጵያዊያን የአርኪዮሎጂ ተልዕኮ መሪ የነበረው አንፍሬ፤ ትንሽ ቀደም ብሎ፣ የጥድፊያ አሰሳ ተደርጎ፤ “ . . . ከግንቢ ፍጹም የተለዩ ዓይነት” [፵፫] እንዳሳዩ አረጋግጦለታል። አንፍሬና ሪኮ፤ የ “ሲሬ ከተማን” ነው የጠቀሱት ብንል፤ በግልጽ ምንም ዓይነት ጥልቅ የሆነ ጥናት ማድረጉ አምልጧቸዋል። ቦታው እንደሚታየው ፍጹም ያልተቆፈረና ያልተጠና ነበር። በደራሲዎች ዕውቅናም፤ ጥናቱ ለዕትመትም ፍጹም አልበቃም።

የ “ሲሬ ከተማ”፤ ቁልቁለቱ ሳይጣድፍ ወደ ደቡብ ምዕራብ ራቅ ብሎ የሚያዘቀዝቅ፤ አንድ የጉብታ አናት፤ ( አደረ ተራራ፤ ከባሕር ከፍታ በላይ ፳፩፻፴፰ ሜትር ) አለው። ጉብታው፤ ምንም እንኳን በብዙ ቦታዎች ላይ በአንጻሩ ስጥ ሜዳ ቢሆንም፤ በአካባቢው ገዝፎበታል። ወደ ደቡቡ ወለል ያለ ሜዳ በዘገምታ ወርዶ፤ ደብረ ዘይት አጠገብ ወደ ሃዳ ወለል ያለ ምድር ይለጠጣል። በምዕራብ በኩል፤ የቤልቤላ ወንዝ ጥበቃ ይሠጣል፤ የውሃ ፍላጎትንም ያሟላል። [፵፬] እንዲያ ቢሆንም ግን፤ ልክ እንደ “ሲሬ ከተማ” ቀለል ያለ

---

፵፩ ፍራንስዋ-ዣቬር ፉቪሌ-አይማር ከየፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናቶች ማዕከል (ኤኤፍኢኤኢ) አዲስ አበባ፤ ቦታውን ሄደው ዓይተው፤ ባጠቃላይ የቀድሞ ቦታ መሆኑን አረጋግጠዋል። Francois-Xavier FAUVELLE-AYMAR from the CFEE, Addis Ababa visited the site and confirmed its generally ancient appearance.

፵፪ የመልከዐ ምድር አቀማመጥ፤ Geographic position: 8o 52’24”N; 39o03’04”E.

፵፫ ኤል. ሪቺ ( ፲፱፻፸፮፣ ገጽ ፻፺፮ ) L. RICCI (1976: 196).

፵፬ በሚያዝያ ፳፻፫፤ ከደረቁ የበጋ ወራት መጨረሻ ላይ እንኳን፤ ለአካባቢው ብርቅ የሆነውን፤ የቤልቤላ ወንዝ አልደረቀም ነበር! ከቤልቤላ ወንዝ ጎን፤ ከ “ሲሬ ከተማ” ሰሜን፤ ፶፪ ሜትር የሚሆን ርቀት ላይ፤ ብርቱ ትኩስ ፍልውሃ (ትፍው)፤ ባስተማማኝነት በበጋው ወቅት እንኳን ይሠጣል። በትክክል ምንጮችና ትኩስ ውሃ ብርቅ በሆነበት በዚህ አካባቢ፤ ይህ የጥቅም ብልጫ ነው።

መሻገሪያ ( መልካ ) ( ፎቶ ፲፩ ) የቤልቤላን ወንዝ መሻገር ያመቻል። እናም፤ ለዋናው ከምሥራቅ ምዕራብ ለሚወስደው መንገድ እና በሰሜን ወደ ደብረብርሃን ለሚወስደው መንገድ፤ ሌላ ብርቱ ወንዞችን ሳይሻገሩ ለማለፍ ክፍተት ይሠጣል። ፲፫ ኪሎ ሜትር የሚሆን ወደ ደቡብ ራቅ ብሎ፤ ቤልቤላ፤ ከአካባቢው የጅረቶች መፍሰሻ ሁሉ፤ ወደ ጎላው ወደ ሞጆ ወንዝ ይፈሳል። ፯ ኪሎ ሜትር የሚሆን ወደ ሰሜን ምዕራብ ብዙም ሳይርቅ፤ በየረር ተራራ ሰሜናዊ ቁልቁለት ከወደ ላዩ በኩል ተቆፍሮ የተገኘው የመካከለኛው ዘመን፤ የጊንቢ ቤተ ክርስትያን ( በግምት ፲፬ ኛው እስከ ፲፫ ኛው ክፍለ ዘመን ) ይገኛል።

ከሰማይ የተነሳው ፎቶ ( ስዕል ፳ን ይመለከቱ ) አሁንም ቁልጭ ብሎ በገሃድ ያለውን፤ በጉብታው አናት ላይ፤ ጥንድ ዙር ጥምጥም በግምብ የታጠረውን የ “ሲሬን ከተማ” ያሳያል። እኒህ አሁንም ከፍ ያለ፤ ከደንጋይና ካፈር እስከ ፩ ሜትር ተኩል የሚደርስ ቁመት ያላቸው የግምብ አጥሮች፤ ከሩቅ ይታያሉ።

ሆኖም ግን፤ ከጉብታው አናት ላይ ካለው የግምብ አጥር ቅንብር ውጪ፤ ሌሎች የ “ሲሬ ከተማ” የጥንት ቅንብሮች፤ ለመጀመሪያ ዕይታ ግልፐ አይደሉም። አካባቢውን አተኩረው ሲያጠኑ ብቻ ነው፤ መኖራቸው የሚታወቀው። በጥንቃቄ የታቀደና የራሱ የሆነ የግምብ አጥር አሠራር ቅንብር፤ በማለት ብቻ የሚተረጎም፤ ከጉብታው አናት ( የላይኛው ከተማ ) አልፎ ወደ ደቡባዊ ምዕራብ ዝርግ ትከሻው ( ደቡባዊ ከተማ ) የተንጣለለ፤ አስገራሚ የተለያዩ ቁሶች ናሙና አበጅተዋል። ጠቅላላው የ “ሲሬ ከተማ” መሬት፤ በግምት ፲፰ ሄክታር ነው ( ስዕል ፱ን ይመለከቱ )።

ከሁሉም በከፋ ተጠቂ ሊሆንበት በሚችለው፤ ከወደ ሰሜን እና ሰሜናዊ ምሥራቅ፤ ጥልቀት ያላቸው መፋሰሻዎችና ሰው ሠራሽ ምሽጎች ቦታውን ይጠብቁታል። ከዚህ አቅጣጫ፤ የጉብታችን አናት የመጨረሻ ደቡባዊ አካሉን የሆነበት፤ አንድ ግዙፍና ረጅም ቁልቁለት ይንጣለላል። ሆኖም ግን፤ የከተማዋ ሁለት በሮች (መ፩) በቀጥታ እዚህ ላይ፤ በስተሰሜን ምሥራቅ፤ ነው ያለው። እናም ወደ ደብረብርሃን ከሚወስደው መንገድና ከቤልቤላ ጅረት (ጅ) ጋር ያገናኛል። ብሎም ወደ የረር ተራራና ጊንቢ ከሚወስደውም መንገድ ጋር ያገናኛል። ምሽጉን በዚህ በኩል አቋርጦ ወደ ውስጥ የሚያስገባው መንገድ አሁንም ይታያል። አጥቂዎችን ለማቆም ጠንካራ መከላከያ ሆነው ከቆሙት፤ በሰሜን ምሥራቅ ካለው ግዙፍ የግምብ አጥር ምሽግ ቅንብርና ከልብ አንጠልጥል አዘቅቱ በተጨማሪ፤ አጠገቡ ያሉት የግምብ አጥር ቅንብሮች፤ መግቢያ በሩን ለመጠበቅ የተጠነከረ የምሽግ ፊት (ምፊ፩) ቅሪቶችን የሚወክል ሊሆን ይችላል።

የቤልቤላን ጅረት (ጅ) አልፈው የ “ሲሬን ከተማ” ከወደ ምዕራብ በኩል ሲቀረቡ፤ አንድም ከተማዋን ማዕከል በዋናው መግቢያ በር (መ፩) ወይንም ከጅረቱ እየመራ፤ የ፪ ሜትር ስፋት ኖሮት፤ ቀጥ ያለ አንጻራዊ ዳገትነት ባለው ሊገባ ይቻላል ( ፎቶ ፲፪ )። ያለ ምንም ጥርጥር፤ መንገዱ የቅርብ ጊዜ አይደለም። የጉብታውን አለታማ ክፍል በመጥረብ ለመንገዱ ማለፊያ ለማበጀት፤ ጥረቶች ተደርገዋል። መንገዱ፤ በተለይም ከጅረቱ አጠገብ ከወደ መነሻው በኩል፤ በግምብ አጥሮች ተጠናክሯል። በተጨማሪም፤ ይሄን መግቢያና ጅረቱን ራሱን ለመከላከል፤ የግምብ አጥሮች ተገንብተዋል። በዚሁ ግብ እሳቤ፤ አንድ አነስ ያለ ደልዳላ ቦታ (ምፊ፫)፤ ከጅረቱ በላይና ከመንገዱ መግቢያ ፳ ሜትር የሚሆን ርቀት ላይ፤ ከአለታማው ደንጋይ ተጠርቦ ተነጥፎ፤ በግምብ አጥር ተመሽጎ፤ መግቢያውንና የጅረቱን መቃረቢያ መቆጣጠሪያ ጉድብ ሆኖ አገልግሏል።

ወደ ጅረቱ ከሚወስደው ኸው ያለ ቁልቁለት ጫፍ ሲደርሱ፤ ፪ ሜትር የሚሆን ስፋት ባለው በር በኩል(መ፪)፤ ፪ ሜትር ስፋት ያለው የግምብ አጥር ( አሁን መሠረታቸው ብቻ የሚታየው ) በሚያበጀው

የተገደገዱ ደረጃዎች ይታለፋል (ፎቶ ፲፫)። ፲ ሜትር የሚሆን ርቀት በኋላ፤ እንግዳው ወደ ከተማዋ ከመግባቱ በፊት፤ በሌላ የ ፪ ሜትር ስፋት ያለው ግምብ አጥር ውስጥ ማለፍ አለበት። ሁለቱ የግምብ አጥሮች፤ ከወደ ሰሜን በኩል ይዋሐዱና - ሁሌም የጉብታውን አናት ተረር በመከተል - ወደ መግቢያ በሩ (መ፩) ውሕዳቸው ያመራል። ይህ ጠንካራ በሁለት ዙር ጥምጥም ግምብ አጥር በቤልቤላ ወንዝ በኩል ምሽጋ፤ መጀመሪያ ሲታይ፤ ከራሱ ከወንዙ በቂ ጥበቃ ይገኛል ብሎ ሰው ስለሚያስብ፤ ያስገርማል። ሆኖም ግን፤ በበጋው ወራት ወንዙን በቀላሉ ለመሻገር ስለሚቻልና በዚህ በኩል የጉብታው ቁልቁለት ዳገቱ ያን ያህል አስቸጋሪ ስላልሆነ፤ ወስነው የመጡን ወራሪዎች አያግድም። በመጨረሻ ብቻ፤ ለ "ታችኛው ከተማ" ምዕራባዊ ጎን፤ በደቡብ በኩል ፸ ሜትር የሚሆን ራቅ ብሎ፤ የቤልቤላ ወንዝ ፲ ሜትር ወደታች ተዥጎድጉዶ ቀጣታ ሲወርድ፤ ዳርና ዳር ስንጥቆ የሸለቆውን ገደላማ ጎኖችን ስላበጀላቸው፤ ተፈጥሮ መከላከያ ለግሳቸዋለች (ፎቶ ፲፬)።

ሜዳማው የ "ታችኛው ከተማ"፤ በዋናው የቁልቁለት ተረተር መዳረሻ ጠመዝማዛ ላይ ነው። ካነሳሱም ሳይጎረብጥ፤ ታች ወዳለው ደቡባዊው ዝርግ መሬት ለጥ ብሎ ተዘርግቷል። በዚህ ደካማ ጎን በኩል በቂ ጥበቃ መኖሩን ለማስረገጥም፤ አንድ፤ ፲ ሜትር ስፋትና ፬ ሜትር የሚሆን ጥልቀት ያለው ምሽግ (ም)፤ በእሳተ ጎመራው ውጤት መሬት ላይ ተቆፍሯል (ፎቶ ፲፭)። ይህ የተቆፈረ ምሽግ፤ በደቡቡ መግቢያ በር (መ፫) በኩል፤ ወደ ከተማዋ ለመግባት በር ሠጪም ሊሆን ይችላል። አንድ ጎብኚ፤ ጎን ለጎን ሆነው በሚሄዱ የግምብ አጥሮች፤ አሁንም በደንብ በንክብካቤ የተያዘና የሚታይ ቀልጠፍ ያለ የምሽግ ቅንብር፤ ከማለፉ በፊት፤ በጥንድ ጉድቦች ( ጉ፫ እና ጉ፬ ) ማለፍ አለበት።[፴፭]

ከዚህ ደቡባዊ የከተማው በር፤ አንድ የጥንድ ግምብ አጥር ቅንብር፤ በተለያዩ ሁለት ደልዳላ ቦታዎች ላይ፤ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ይዘረጋል። ይህ ቅንብር፤ በደቡብ ምሥራቅ በኩል በጉድባ (ጉ፪) ተጠናክሮ፣ "ላይኛው" እና "ታችኛው ከተማ" በሚገናኙበት የከተማዋ ዕምብርት ላይ የሚገኝ አንድ ፎቅና (ፎ) ሌሎች የግምብ አጥር ቅንብሮች ወዳሉት አንድ በዕውቅ የተሠራ ምሽግ ይወስዳል። ይህ እነፃ በጣም ባመዛኙ፤ የጉብታው ቁልቁለት ረጋ ብሎ በሚያዘቀዝቅበት ደቡብ ምሥራቅ በኩል ለሚገኘው፤ ከዚህ ቀረብ ላለው ፬ኛ በር፤ መጠበቂያ ይሆናል። ከዚህ ቦታ ተነስቶ፤ አንድ ነጠላ የግምብ አጥር ወደ ደቡቡ ግምብ አጥር፤ በስተምሥራቁ በኩል ይነጉዳል። በጥቅሉ፤ እኒህ በምሥራቅ በኩል ያሉ የግምብ አጥሮች፤ በሰሜን ወይንም በደቡብ እንዳሉት የግምብ አጥሮች የሚያስደንቁ አይደሉም። ይህ እንዲሆን ያደረገው፤ በአብዛኛው ክፍል፤ አንድ በጣም በቀጥታ ወደታች ያሽቆለቆለ አዘቅት፤ ይሄኛውን የ "ሲሬ ከተማ" ወገን አስቸጋሪ ያደረገበት ሀቅ ስላለ ነው።

መካከለኛው የ "ሲሬ ከተማ" ቦታ፤ አሁንም እንዳለ ያለ የግምብ አጥር ቅንብር (ቅ)፤ በእንክብካቤ ከተጠበቀው ቁመቱ ( እስከ ፩ ነጥብ ፭ ሜትር ድረስ ) አኳያ፤ አሁንም ከሩቅ የሚታየው ይገኝበታል ( ስዕል ፰ን ይመለከቱ )። ከመሐል በሚገኘው የግምብ አጥር ውስጥ (በ ፯ ሜትር የሚሆን የታቀፈ መሬት (ስኩዌር))፤ ምናልባትም ሕንፃዎችን ለመገንባት መሠረት የሚሆኑ፤ ተልቅ ያሉ ባለ አራት ማዕዘን ጡቦች ተብሎ ሊወሰድ የሚያስችል፤ ረቀቅ ያለ የግንበኝነት ሙያ ተላብሰዋል። (ፎቶ ፲፮)

---

፴፭ ከ መ፫ ላይ፤ የተለያዩ ሕንፃዎችና በተላየ የሰፈራ ደረጃ ላይ ያሉ ሁኔታዎች በግልጥ ይታያል። ግዙፍ የሆነ የግምብ አጥር መሠረቶች፤ ቀለል ካሉት ሥር ተጋድመዋል፤ ( ፩ ሜትር የሚሆን ስፋት ያላቸው )፤ ያኋለኞቹ አሁንም አንጻራዊ እንክብካቤ ተደርጎላቸውና ፲ ሜትር አስከሚሆን ቁመት አላቸው። ( ፎቶ ፳, ፳፩ )

አሁንም ካለበት የልተነቃነቀና በግልጥ የሚታይ፤ ፮ ሜትር በ ፱ ሜትር በሚሆን በአራት ማዕዘን የተዘጋጀ የሕንፃ ጡቦች አለ (ፎቶ ፲፮)። ሆኖም ግን፤ አካባቢው፤ ምናልባት በአካባቢው ነዋሪዎች ለሕንፃ ሥራ ምመጠቀሚያ ፍልጋ፤  በከፊል ተነካክቷል። በሁሉም አካባቢ፤ ጎላ ብሎ የሚታይ የቀድሞ የሕንፃ ቅንብር ለመኖሩ፤ የተበታተኑ ተመሳሳይ ጥራት ያላቸው ጡቦች በቂ ማስረጃ ይሠጣሉ። ቅንብሩን እና ሌላ የአርኪዮሎጂ ማስረጃ፤ በዚህ ዕውቅ ቦታ ሊወጣ ስለሚችል፤ ግልጥ እንዲሆኑ፤ የቁፈራ ጥናት ያስፈልጋል።

በጉብታው አናት ላይ ባለው ጥንድ የግምብ አጥር ዙሪያ ያለው ቦታ፤ ጥቅጥቅ ባለ የሰፋሪዎች የሸክላ ሥራ፣ የወፍጮ ስባሪዎች፣ የባልጩት ስብርባሪዎች ተሞልቷል። [፵፮] አንድ ቦታ ላይ ያለ ገጽታ፤ ከሸክላ ሥራዎችና ከአጥንት ስብርባሪዎች ጋር፤ ከሰል አብሮ ተጓድኖ ይታይበታል። በጉብታው አናት ማዕከል ደቡብ ምዕራብ በኩል፤ አንድ የሚደነቅ ግኝት፤ ግልጥ በሆነ መንገድ በዛ ያለ ሕዝብ ቦታውን ሰፍሮበት እንደነበር ያረጋግጣል። ይሄውም፤ አንድ በእሳተ ጎመራው የተፈጠረ በጣም ትልቅ ደንጋይ፤ ለወፍጮነት ተጠርቦ፤ ሶስት የተለያዩ ወፍጮዎች ተወቅረውበታል (ፎቶ ፲፰)። ሌላ የ “ላይኛው ከተማ” የሚያስደንቅ ገጽታ፤ ከጉብታው አናት ሰሜን ምሥራቅ የተተከለ፤ አንድ ግዙፍ ክብ የግምብ አጥር (ክግ) ነው። ትልልቅ ደንጋዮች፤ እዚህ ላይ ፵ ሜትር የሚሆን የወገብ ልክ ያለው ግማሽ ክብ ሠርተዋል። በግልጥ ከክቡ ውስጥ ተፈልፍለው ወጥተው፤ ለጥ ያለ ሜዳማ ቦታ ፈጥረዋል።

“የታችኛው ከተማ” የተቀመጠበት ደልዳላው የመሬት ከፍታ፤ በግምብ አጥር ቅንብሩ በኩል ይሄነው የሚያስብ አይደለም። ሆኖም ግን፤ ይሄ አካባቢ - ምንም እንኳን ከመካከለኛ የጉብታው አናት ባጠቃላይ አነስተኛ የሆነ የቀድሞ ሰፈራ የአርኪዮሎጂ መረጃዎችን ቢለግስም፤ ( የሸክላ ሥራዎች፣ ስባሪ ዝርግ መገልገያ ነገር፣ ወዘተ ) - ይህ የከተማው ክፍል በደንብ የታቀደና መልክ ያለው መሆኑን የሚያመለክቱ፤ የሚቆጠሩ የሕንፃ ቅንብር ማከናወኛዎችን አሳይቷል። ይሄን ቦታ ከደቡብ መግቢያ በሩ (መ) ሲቀርቡ፤ ዛሬም መሠረታቸው በሚታይ የመግቢያ በር ወይንም ደጃፍ (ደ) በኩል፤ አንድ የግምብ አጥር ያልፋሉ (ፎቶ ፲፱)። በ “ታችኛው ከተማ” ተረተር ትከሻ ላይ ( በ “ላይኛው ከተማ” አንዳንድ ክፍሎችም ) ያሉት የግምብ አጥር ቅንብሮች ፍርስራሾች፤ የከተማ ቅንብር እንደነበር ይጠቁሙም ይሆናል።

የአፍ ታሪክ፤ ጥቂት የሆነ የ “ሲሬ ከተማ” ን እውቀት የጠበቀልን ይመስላል። ከጉብታው ጎን የሚኖሩ ሰዎች፤ ( በጉብታው አናት ላይ ላይ ያለው ከአሕመድ ግራኝ ጋር ከተያያዘው ደንጋይ ሌላ ) ስለቦታው ታሪክ ጥቂት እውቀት አያላቸው ይመስላል። ሪቺ በዘገባው፤ [፵፯] ከጊንቢ የጥናት ቦታ አካባቢ ያሉ ሰዎች ( ወደ ሰሜን ሞዕራብ ፮ ኪሎ ሜትር የሚሆን )፤ አንድ የነገሥታት መንደር፤ ከሁለቱም፤ ከአፄ ዘረ ያዕቆብና ከአፄ ልብነ ድንግል [፵፰] ጋር የተሳሰረ፤ ከጊንቢ ቤተ ክርስትያን ብዙም ሳይርቅ፤ አለ ብለው ያምናሉ፤ ሲል አስፍሯል። በአፍ ታሪክ ባህሉ የተዘከረው የሰፈራ ቦታ የ “ሲሬ ከተማ” ይመስላል።

ሌላ ልብ የሚስብ ፍንጭ እንደገና፤ ከ ዲ’አባዲ [፵፱] ይገኛል። ዲ’አባዲ ሲዘግብ፤ አንድ “የዘረ ያዕቆብ

---

፵፮ በተጨማሪ ጥቂት ብርቅ የሆኑ የባልጩት ስል መቁረጫዎች፤ የደንጋይ ዘመን ወደስተመጨረሻው፤ በዝዋይ ሐይቅ ከተገኙት ጋር ተመሳሳይ ዓይትነትና አጠራረብ ያላቸው፤ ይገኛሉ። (ኤፍ. ቦን እና ተባባሪዎቹ፤ ፳፻፮፤ ገጽ ፹፮ እስከ ፻፳፱ ) (F. BON *et al*., 2006: 86-129). ይህ፤ በጣም አመቺ ሆኖ በተቀመጠው ጉብታ ላይ፤ ቀደም ብሎ ለረጅም ዘመናት፤ የሰፈራ ባህል መኖሩን ይጠቁም ይሆናል።

፵፯ ኤል. ሪቺ (፲፱፻፸፮፤ ገጽ ፻፺፮ ) L. RICCI (1976: 196).

፵፰ ሪቺ፤ ያካባቢው ሰዎች፤ ከግንቢ ብዙም ሳይርቅ፤ በጉብታው አናት ላይ የነበረ፤ የነገሥታቱ “የማዕድ ቤት” (“cucine della dimora reale”) እያሉ ያወራሉ ሲል ዘግቧል።.

፵፱ ኤ. ዲ’አባዲ (፲፰፻፺፤ ገጽ ፪፻፺፱ ) A. D’ABBADIE (1890: 299).

የጥንት ከተማ"፤ "ancienne ville de Zar-a Ya'iqob" ከየረር ተራራ ላይ ("sur le Mt Harrar") ካለው የባሪያ መሸጫው ሮጌ በተቃርኖ፤ ከሃዳ ሜዳማ መሬት [፴] ከፍ ብሎ፤ ብሏል። ይህ ገለጣ፤ የሲሬ ከተማን በትክክል ይገጥማታል።

### (መ) ሌሎች ስፍራዎች

ከላይ ከቀረቡት ስፍራዎች ጎን፤ ጥናቱ፤ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ጥቂት አነስተኛ የሆኑና ብዙም ዕፁብ ድንቅ የማይባሉ፤ ጥንታዊነት ያላቸው ቦታዎችን አስሷል። ሙሉ ገጽታውን ለመሥጠትና ለወደፊት ጥናቶች እንዲያመች፤ የነዚህን ስፍራዎች ዝርዝር ጠቅለል አድርገን ከዚህ አስከትለናል ( አብዛኛዎቹ ስፍራዎች የጉግል ኧርዝን በመጠም ሊ "ጎበኙ" ይችላሉ )።

- በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት ከሚገኘው ከተመሸገው የጉብታ አናት ፫ ኪሎ ሜትር የሚሆን፤ ከመናገሻ "ዙፋን የሚጫንበት፤ ተራራ በግምት ፫ ኪሎ ሜትር የሚሆን ርቀት ላይ፤ ግዙፍ በለ አራት ማዕዘን፤ ፻፶ በ ፻ ሜትር የሚሆን የግምብ አጥር እና ምናልባትም ከፍታ ባለው ዳገት ላይ የሕንፃዎች ፍርስራሽ ( ፳፭፻፭ ሜትር ከባሕር ወለል በላይ ) በወጨጫና በእንጦጦ ተረተሮች መካከል አንዣቦ ይገኛል። መልከዓ ምድር አቀማመጡ፤ (9o00'43.50"N; 38o37'55.38"E) ላይ ነው።
- ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው ስፍራ ለጥቆ ወደ ምሥራቅ፤ ፪ ነጥብ ፬ ኪሎ ሜትር ወደ ምሥራቅና ከአዲስ አበባ ከፍ ብሎ፤ ፳፫፻፰ ሜትር ከባሕር ወለል በላይ፤ አነስተኛ የጉብታ አናት፤ በጣም በተሸረሸረ ፳፰ ሜትር የሚሆን የወገብ መቀነት ርዝመት ያለው ክብ የግምብ አጥር፤ ከሁለት የጥንት የመቃብር ቦታዎች (?) ጋር አለ። መልከዓ ምድር አቀማመጡ፤ (9o00'42.29"N; 38o39'12.60"E) ላይ ነው።
- በግምት ፫ ኪሎ ሜትር በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት ከሚገኘው ከተመሸገው የጉብታ አናት ደቡብ ምሥራቅ፤ በ ፳፩፻ ሜትር ከባሕር ወለል ከፍታ ላይ፤ ግዙፍ የግምብ አጥር ክብ፤ የወገብ መቀነት ርዝመቱ ፻ ሜትር የሚሆን፤ ከጥቂት የውስጥ የግምብ አጥር ቅንብሮች ጋር፤ በአንጻራዊ ሲታይ ደልዳላ በሆነ ቦታ ይገኛል። መልከዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8o57'44.58"N; 38o38'12.33"E) ላይ ነው።
- ከየረር ተራራ ደቡብ፤ በታችኛው ጉብታዎች ሰንሰለቶች፤ ወደ ዱከም ወንዝ፤ ከባሕር ወለል በላይ ፳፩፻ ሜትር ከፍታ ያለው፤ በግምት ፭ ግዙፍ የግምብ አጥር ክቦች፤ ፭ ሜትር የሚሆን የወገብ መቀነት ርዝመት ያላቸው፤ በዚያ ጊዜ በነበረው አሠራር ዓይነት ካካባቢው ምድር ዝቅ ያናለ፤ ጠንከር ብሎ የተገነባ ወለል ይገኛል። መልከዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8o50'08.19"N; 38o55'11.89"E); ላይ ነው። ከዱከም ከተማ ቀጥሎ፤ ፳፪፻ ሜትር ከባሕር ወለል በላይ ከፍ ባለ የጉብታ አናት ላይ፤ ከሃዳ ዝርግ መሬት በመለጠቅ ከፍ ብሎ፤ ፲፰ ሜትር የሚሆነው ብቻ የሚታይለት የግምብ አጥር ግዙፍ ፍርስራሾች አሉ። መልከዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8o48'42.16"N; 38o55'10.14"E) ላይ ነው።
- ከየረር ተራራ ዋናው ጫፍ ለጥቆ በምሥራቅ በኩል እና ከዱከም ወንዝ መመንጫ አጠገብ፤ ከባሕር ወለል በላይ ፳፫፻፶፰ ሜትር ከፍ ባለ ዳገት ላይ፤ በግምት ፰ የግምብ አጥር ግዙፍ ክቦች፤

---

፴ በየረር ተራራ እንደሚኖሩት ያካባቢው ሰዎች አገላለጥ፤ ሮጌ ተብሎ የሚጠራ አንድ የገበያ ቦታ፤ ከየረር ተራራ በቀጥታ ሰሜንና ከሐሙስ ገበያ ደቡብ ምዕራብ በትክክል አለ። ይህ የመልከዐ ምድር አቀማመጥ፤ መስመር፤ ዲ'አባዲ ካሰፈረው ዘገባ ጋር አንድነት አለው። የሃዳ ስጥ ሜዳ፤ በሞጆና በዱከም ወንዞች መካከል ያለው ዝርግ ቦታ ነው። ከ "ሲሬ ከተማ፤ ጉብታ አናት ደቡብ፤ የሃዳ ስጥ ሜዳ ይጀምራል።

፲ ሜትር የሚሆን የወገብ መቀነት ርዝመት ያላቸው አሉ መልክዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8ο54’09.48”N; 38ο56’11.53”E) ላይ ነው። በትይዩ ካለው ሌላ ጉብታ ላይ፤ የሰፈራ ቦታ በጣም የበዙ ቅሪቶች፤ ( የሸክላ ሥራዎች፣ የወፍጮ ደጋዮች ) ተገኝተዋል። መልክዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8ο54’10.67”N; 38ο56’32.67”E) ላይ ነው።

- ከደብረዘይት ደቡብ ምሥራቅ፤ ከሆራ ሆዳ ጀርባ፣ በበዴ ገባቤ አካባቢ ባለ አንድ ትልቅ የእሳተ ጎመራ አናት ደቡባዊ ምሥራቅ ደንደስ ላይ፤ ከባሕር በላይ ፳፪፻፹ ሜትር ከፍታ፤ መልክዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8o40’32.03”N; 38o57’17.38”E) ላይ፤ ጥንድ የግምብ አጥር ሕንፃ ቅንብር (የወገብ መቀነት ርዝመቱ በግምት ፲ ሜትር ) በቅርብ ጊዜ ያካባቢው ነዋሪዎች ደንጋዮቹን ለመጠቀም፤ ድራሹን ሊያጠፉት የነበረ አለ። ያካባቢ ነዋሪዎች፤ ሁለቱ ሕንፃዎች በዳግማዊ ሚኒሊክ ዘመን አካባቢውን በባለቤትነት የያዙ የአንድ የመሬት ከበርቴ (ራስ) ነበሩ ብለው ያምናሉ። ይሄ ግምት አሁን እንዲህ ከመውደሙ በፊት የነበረውን አያያዝ ሲያጤኑት፤ እውነትነቱ ሥር አለው።
- ለሞጆ ወንዝ ለጥቆ በምሥራቅ በኩል ለሚገኝ አንድ ስፍራም እንዲሁ ማለት ይቻላል፤ ወፉ ተብሎ በሚጠራ አንድ ጉብታ በምሥራቁ ባለው ቁልቁለት፤ ፳ ፻ ሜትር ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ ላይ፤ መልክዓ ምድር አቀማመጡ፤ (8o49’40.05”N; 39o05’51.35”E) ላይ፤ በከፍል ግዙፍ በሆነ የግምብ አጥር የተከበበ፤ አሁንም አንድ ውብ የሆነ የደረጃ እንፃ ያለው የጥንድ የግምብ አጥር ሕንፃ፣ ባጠገቡ ሌላ የክብ ሕንፃ፣ በተጨማሪ ደግሞ ሁለት ሌሎች ሕንፃዎች፤ ምናልባትም ለዕቃ ማስቀመጫ የሚያገለግሉ፤ ሁሉም ቅንብሮች አሁንም በአንጻሩ ደህና የተጠበቁ፤ የግምብ አጥሮቻቸው አሁንም እስከ ፮ ሜትር ከፍታ ኖሯቸው ቆመው የሚገኑ፣ ይህም ስፍራው እስከ ፲፱ ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ የ(ጦር/አስተዳደር ) ቦታ ይወክላል ብሎ ለመገመት ያመራል። [፵፩]

፵፩ ፍራንስዋ-ዣቬዥ ፋቪል-አይማር፤ ከየፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናቶች ማዕከል (ሲ. ኤፍ. ኢ. ኢ.) አዲስ አበባ፤ ቦታውን ቦታውን ጎብኝተው፤ ባጠቃላይ የቀድሞ ቦታ መሆኑን አረጋግጠዋል።.

## *መደምደሚያ*

በረራ ወይንም ባደቀ በዚህ ጥናት ሊታወቁ አልቻሉም። ማናቸውንም የታዩ ቦታዎች፤ የሁለቱ ከተሞች ናቸው ብሎ በርግጠኝነት መውሰድ አይቻልም። የዚህ ምርምር ጥናት መነሻ ግምቶች፣ (ከግምብ አጥር ቅንብር ጋር በጉብታ አናት ላይ መሆን ) ትክክል ላይሆን ይችላል። እንዲህ ያሉ ከተማዎች በጣም ደልዳላ ከሆኑ ቦታዎች ላይ ተቀምጠው ቢሆን ኖሮ፤ በዝናብ ውሃ መሸርሸር ምክንያት ቅንብሮቹን ደለሉ ይቆለልባቸው ነበር። ቢሆንም ግን፤ ከይፋት የእስልምና ተከታዮች የ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን ከተሞች ጋር ንፅፅሩ፤ በጣም የቀረበ ዘመን ያላቸው የ፲፬ኛውና የ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የሕንፃ ቅንብሮች ጎላ ብለው የሚታዩ ዱካዎች መተው አልነበረባቸውም ብሎ ማመን ታስቸግራል። የሚመስለው፤ ከ፲፮ እስከ ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ የክርስቲያኖች "ከተሞች"፤ የግምብ አጥርና የደንጋይ ቅንብሮችን ፍጹም አልተጠቀሙም ነበር፤ ነገር ግን፤ የግንድና ጭቃ ግድግዳ አጥሮችን ብቻ ተጠቅመው፤ እኒህም ይህ ነው የሚባል ቅሪት አልተውም።

ይህ እንዳለ ሆኖ፤ በፍራ ማውሮ ካርታ እንደተመለከተው፤ በረራ በየረር ተራራና በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት መካከል ነበረች ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት አለ። የዚህ ምርምር ጥናት ውጤት፤ ከአሁኑ ዘመን ቀደም ብሎ በደቡብ ሸዋ የነበሩ የሰፈራ ቦታዎች፤ በዋናነት ከ፳፻ እስከ ፳፫፻ ሜትር ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ ባላቸው ጉብታዎችና አምባዎች፤ ለም የርሻ መሬት፣ ዋነኛ የተባሉ በሺታዎች አለመኖራቸው፤ በቂ የዝናብ ፍሳሽ፣ ከቀሪው የአቢሲኒያ ግዛት ጋር ጥሩ ግንኙነት ለማድረግ ተመቺነቱ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን አረጋግጧል። እዚህ፣ በሰፊው፣ በእንጦጦ፣ የረር ተራራና በወጨጫ ተራራ ሰንሰለት መካከል መጠነኛ ጉብታነት ባላቸው አምባዎች፤ በረራም፤ የዞርዚ መረጃ የበረራን "ወይና ደጋማ" የአየር ጠባይ እንደሚያትተው፤ እዚህ ቦታ ላይ መሆን አለባት።

ጥናቱ በተካሄደበት ከሞላ ጎደል ሁሉንም ዋና ዋና የተባሉት ጉብታዎችና ዳገቶች ከተጎበኙ በኋላ፤ በረራ በደራ፣ ጠንካራ ምሽግ የተሠራለት የጉብታ አናት፣ ላይ አልታነፀችም። በብዛት ሆነ ብሎ መገመት የሚቻለው፤ "ከተማዋ" በተወሰነ የግምባታ ቅንብር ብቻ ( እንደ የአቢሲኒያዊያን ነገሥታት "ተንቀሳቃሽ ዋና ከተሞች" ) በዋናነት በቀላሉ ተሰባሪና በስባሽ ነገሮች የተሠራች መሆኗ ነው። በዚህ ጉዳይ በኩል፤ በረራ፤ ሁሉን የሚሸፍን የመስክ ጥናት በአካባቢው ለማድረግ፤ ከቁሳቁስ እጦት የተነሳ የመካሄድ ዕድል ስለሌለው፤ በአጋጣሚ ብቻ ነው ልትገኝ የምትችል። በዚህም አለ በዚያ፤ የ"ከተማ" ጠቋሚ ምልክቶች አለመኖራቸው ግልጥነቱ ( ጎላ ያለ አቀማመጥ፣ የግምብ አጥሮች፣ ምሽጎች ) ለወደፊቱም ከባድ ትኩረት የተሠጠው የመስክ ጥናት ቢደረግም እንኳን፤ ለበረራ ትክክለኛ መገኛ ቦታ፤ የሚያረካ መረጃ ለማቅረብ አስቸጋሪ ያደርገዋል። "ከተማ" ዋ፤ በጣም ባመዛኙ፤ "ሚስጥር" ሆና ትቆያለች።

በወጨጫ ተራራ ሰንሰለት የሚገኘው የተመሸገው የጉብታ አናት፤ በጣም ባመዛኙ የመካከለኛው ዘመን ከተማ መቀመጫ አይደለም፤ የሕንፃ ቅንብሮችና የሸክላ ሥራዎች አለመኖር፤ በተጨማሪም ዘዋራና ከሞላ ጎደል አስቸጋሪ ቦታነቱ፤ ከዚህ የመሆን ዕድል ሂሳብ ያስወጣዋል። በአካባቢው ተንዘራፍጦ የመገኘት ሀቁ ሲታሰብ፤ በፍራ ማውሮ ካርታ ከተመለከተው አምባነገሥት ጋር ምናልባት አንድ ይሆናል። ሆኖም ግን፤ የደንጋይ ሕንፃዎች ቅንብርና ሌላ የሰፈራ ቅሪቶች አለመኖር፤ ከዚህ ግምት በተቃውሞ ይቆማሉ፤ ይህ፤ በቦታው ላይ የግምብ አጥሩ እንደተሠራ፣ ብዙም ሳይኖሩበት፤ እርግፍ አድርገው ጥለውት መሄዳቸውን ማስረጃ ሊሆንም ይችላል። እኒህን ጥያቄዎች፤ የቁፈራ ጥናቱ ብቻ ግልጥ ሊያደርግ ይችላል።

ባደቅ፤ በስተመጨረሻ፤ ከየረር ተራራ ደቡብ ወይንም ደቡብ ምሥራቅ፤ የሆነ ቦታ ላይ መገኘት አለባት። የእስልምና ተካታይ ጦረኞቹ ዱከም ላይ ሰፍረው፤ መሐል ባደቅ ላይ እሳቱን ማየታቸውን በግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ፤ ደግሞም - በዚሁ የመረጃ ምንጭ ሂሳብ - የአቢሲኒያው ንጉሥ፤ ከእስልምና ተከታዮች ኃይል ጋር፤ ከየረር ተራራ ደቡብ፤ በሽምብራ ኩሬ ግጭት ሲያደርጉ፤ እሳቸው ከባደቅ፤ ከወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መጡ፤ እነሱ ደግሞ ከዱከም ወንዝ፤ ከምዕራብ በኩል መጡ።[፶፪] ከባደቅ በስተምሥራቅ ይሄ የነገሥታት ሰፈር፤ ከየረር ተራራ ደቡብ ወይንም ደቡብ ምሥራቅ ብቻ ነው ሊቀመጥ የሚችል የሚመስለው። ይሄ አቀማመጥ የመሰለ ብቻ ነው፤ የግራኝን ጦር - ዱከም ወንዝ ላይ ሰፍሮ - ባደቅ ላይ እሳት ሲጎን ማየት የሚያስችላቸው።

በዚህ ጥናት፤ ምሽጎች ያሉት፣ ከወንዝ አጠገብ ያለ፣ በየረር ተራራ ደቡብ/ደቡብ ምሥራቅ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ ያለ፤ አንድ ቦታ ብቻ ነው የተገኘ፤ የ"ሲሬ ከተማ"። ይህ ቦታ በግልጥ፤ የረጅም ዘመን የሰፈራ ቦታነት ተለምዶ አለው። ይሄም በጣም ባመዘነ ጎኑ ከመካከለኛው ዘመን ቀደም ብሎ የጀመረ ይሆናል። አንድ የጥንት፤ እምብዛም መንከባከብ ያልተደረገለት ሰፊ ቦታን ያቀፈ ግዙፍ የምሽግ ቅንብር፤ በግልጥ ለሁለተኛ ጊዜ የጥንድ ግምብ አጥር ቅንብሩን ለማነፅ፤ በጉብታው አናት ላይ እና ሌሎች አነስተኛ ጥንካሬ ያላቸው ምሽጎችን በጠቅላላ በጉብታው ስፍራ ለመገንባት የተጠቀሙበት አለ (ፎቶ ፴ና ፴፩)። በጉብታው አናት ዙሪያ ያሉ ጥቅጥቅ የሸክላ ሥራዎችና ሌሎች ቅሪቶች፤ ሆን ተብሎ የተደላደለ የሰፈራ ወቅት እንደነበረበት ያመላክታል። በጉብታው አናት ላይ ያሉ የሕንፃ ሥራዎች፤ በተጨማሪም በጠቅላላ ጉብታው ስፍራ ያሉ የተለያዩ የቅርብ ጊዜ የሚመስሉ የግምብ አጥር ቅንብሮች፤ የመካከለኛው ዘመን ሊሆኑና፤ የባደቀን ቅሪት ሊወክሉም ይችላሉ። ሆኖም ግን፤ ቦታው ማሲን/ሜሶን ሊሆንም ይችላል። የስፍራው መቀመጫ፤ ለፍራ ማውሮ የዚህ ቦታ ጥቆማ፤ ከሞላ ጎደል በትክክል ይገጣጠማል። የቁፈራ ጥናት ብቻ፤ በየደረጃቸው ያሉ የተለያዩ የሰፈራ ወቅቶችን ግልጥ ሊያወጣና፤ የደለበ ርግጠኝነት ሊያስገኝ ይችላል።

የ "ሲሬ ከተማ" ን መቆፈርና ማጥናት፤ ምናልባትም ስለ ቅድመ መካከለኛው ዘመን ምሽጎች፤ በደቡብ አረቢያ የነበረ የነሐስ ዘመን ባሕል ጥንካሬን መዘከሪያ፤ ብዙ ለመማር ልዩ ዕድል ይፈጥራል። የጥናቱ በጉብታ አናቶች ላይ ትኩረቱ፤ እኒህ በግልጥ ቅድመ መካከለኛው ዘመን የተጠናከረ ጥበቃ የነበራቸው ቦታዎችን እንዲገኙ መርቷል፤ በተለይም እንስላሌ ጢቆ፣ ጋራ ቡሹ፣ ኢቺቼና ምናልባትም በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት የተመሸገው የጉብታ አናትንም፣ የምሽጎቻቸው ጥንካሬና በጣም ውስን እንክብካቤ የተደረገላቸው መሆኑ፤ ቅድመ መካከለኛው ዘመን መሆናቸውን ይጠቁማል። ከክርስቶስ ልደት በፊት ሁለት ሺኛው ክፍለ ዘመን፤ የሴማዊያን ከደቡብ አረቢያ ወደ ኢትዮጵያ ፍልሰት፤ ምናልባት እኒህን የእነፃ ልምዶች ወደ ኢትዮጵያ አስመጥቶ ይሆናል። ሆኖም ግን፤ ስለዚያ ዘመን ያለን ዕውቀት ገና አልተቀናበረም። የ "ሲሬ ከተማ"ን የቁፈራ ጥናት እና ሌሎች የተመሸጉ የጉብታ አናቶችም፤ ስለ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ታሪክ ላለን ዕውቀት፤ እስካሁን እንደ መካከለኛው ዘመኗ በረራና በሷ ዘመን በነበሩ ጓደኞቿ የክርስትያን "ከተሞች" ተዘንግቶ የነበረው ወቅት፤ አስተዋፅዖ ሊያደርግልን ይችላል።

፶፪ ቀረብ ባለው ደብረዘይት ያሉ ነዋሪዎች፤ አሁንም አንድ ሽምብራ ኩሬ ተብሎ የሚታወቅ ቦታ፤ ከየረር ተራራ ደቡብ ካሉት ዝቅተኛ ጉብታዎች ጋር ያዛምዱታል።

## ተጣቃሽ ማስረጃዎች፤ Bibliography

(እኒህን መተርጎሙ ፋይዳ ስለሌለው፤ ሊያውቁ የሚፈልጉ በትክክለኛ ስማቸው ይመለከቷቸው ዘንድ እንዳሉ ትቻቸዋለሁ)


ANFRAY Francis, 1978, « Enselale, avec d'autres sites du Choa, de l'Arsi et un îlot du Lac Tana », *Annales d'Éthiopie*, vol. XI, p. 153-169.

BON F., ASAMEREW DESSIE, MENSAN R., FAUVELLE-AYMAR F.-X., 2006,

« Mission de prospection en archéologie préhistorique (LSA) dans la region des Lacs d'Éthiopie (Koka, Ziway, Langano, Abijata) », *Annales d'Éthiopie*, vol. XXII, p. 86-129.

BREITENBACH F. Von, KEUKOL J., 1962, "Managasha State Farm", *EthiopianForestry Review*, 3-4, p. 18.

CRAWFORD O.G.S., 1958, *Ethiopian Itineraries, circa 1400-1524*, Cambridge.

D'ABBADIE A., 1890, *Géographie de l'Éthiopie*, Paris.

DERAT M.-L., 2003, *Le domaine des rois éthiopiens (1270-1527). Espace, pouvoir et monarchisme*, Paris, Publications de la Sorbonne.

FAUVELLE-AYMAR F.X., HIRSCH B., BRUXELLES L., CHALACHEW MESFIN,

CHEKROUN A., DERESSE AYENATCHEW, 2006, « Reconnaissance de trois villes musulmanes de l'époque médiévale dans l'Ifat », *Annalesd'Éthiopie*, vol. XXII, p. 133-175.

STENHOUSE P.L., 2003, *Futuh-al-Habasha*, *The Conquest of Abyssinia (16th century)*, Hollywood, CA.


GILBERT E.F., 1970, *Mount Wachacha. A Botanical Commentary.*

HIRSCH B., POISSONNIER B., 2000, « Recherches historiques et archéologiques à Meshalä Maryam (Mänz, Éthiopie) », *Annalesd'Éthiopie*, vol. XVI, p. 59-87.

HUNTINGFORD G.W.B., 1989, *The Historical Geography of Ethiopia from the First Century A.D. to 1704*, London.


PANKHURST R., 1960, *An Introduction to the Economic History of Ethiopia*.

RICCI L., 1976, « Resti di antico edificio in Ginbi (Scioa) », *Annales d'Éthiopie*, vol. X, p. 177-201.





**ስዕል ፩** ስፍራዎቹ ያሉበት ካርታ ( የኢትዮጵያ ካርታ፤ ውክልናው፤ ፩ ለ፪፻፶፼፤ አቃቂ በሰቃ/ናዝሬት፤ ኢ. ኤም. ኤ፤ ፲፱፻፺፯ / ፲፱፻፺፭ ) ነጭ መስመሮች፤ የጥናቱ ቦታ ደንበሮች።

**Fig. 1** – Location map (based on Ethiopia 1:250.000, Akaki Beseka/Nazaret, EMA, 1997/1995). White lines: boundaries of surveyed area.





**ስዕል ፪** ከፍራ ማውሮ ካርታ የተወሰደ፣ በክራውፎርድ ተቀድቶ የተነደፈ፤ እንደገና በደራሲዎቹ የተሳለ፤

**Fig. 2 –** Excerpt from Fra Mauro's map, re-plotted by Crawford, redrawn by the authors




**ስዕል ፫** የመገናኛ ማዕከል ይሆናል ተብሎ የተወሰደው ቦታና በአካባቢው ዋና የአርኪዮሎጂ ስፍራዎች፤


**Fig. 3 –** The area under consideration as a crossroads, and main archaeological sites known in the area




ባወበከ = ከባሕር ወለል በላይ ከፍታ


**ስዕል ፬** በወጨጫ ተራራ ሰንሰለት ላይ ያለው ምሽግ መገኛ ቦታ ( በኢትዮጵያ ውክልናው፤ ፩ ለ፶፼፤ አዲስ አበባ፤ ደቡብ ምዕራብ፤ ኢ. ኤም. ኤ፤ ፳፻፮ )

**Fig. 4** – Location of the fortification on the Wechecha Range (based on Ethiopia 1:50.000, Addis Ababa S.W., EMA, 2006)





**ስዕል ፭** በወጨጫ ተራራ ሰንሰለት ላይ ያለው የምሽግ ቅንብር ( ውግ = የውጭ ግምብ፣ ከግ = ከፊል ግምብ፣ ክግ = ክብ ግምብ፣ መ = መግቢያ፣ ጉ = ጉድባ፣ ም = ምንጭ )

**Fig. 5 –** The fortification system on Wechecha Range (OW = Outer Wall, SW = Section Wall, CW = Circle Wall, E = Entrance, B = Bastion, S = Spring )





**ስዕል ፮** በእንስላሌ ጢቆ ያለው የተደለደለው የጉብታ አናት (መ = መግቢያ፣ ደከ = የደንጋይ ክቦች፣ ግ = የግምብ አጥር (ከግ = ከፊል ግምብ + ውግ = ውጭ ግምብ)፣ ም = ምሽግ

**Fig. 6 –** The terraced hilltop at Insilale Tiko (E = Entrance, SC = Stone Circles, W = Section Wall & Outer Wall, T = Trench)





**ስዕል ፯** የ "ሲሬ ከተማ" በየረር ተራራ
( ባወከበ = ከባሕር ወለል ከፍታ በላይ )

**Fig. 7 –** The "City of Sire" at Mt Yerer




**ስዕል ፰** የ“ሲሬ ከተማ”። ከ ፲፱፻፸፱ ዓ. ም. የተገኘ የሰማይ ላይ ፎቶግራፍ፤ የኢትዮጵያ ካርታ ቀራጭ ድርጅት (ኢካቀድ) ከምንጩ በ ፩ ለ ፶፼ እንዲያድግ ተደርጓል።

**Fig. 8** – The “City of Sire”. Aerial photo from 1979, Ethiopian Mapping Agency (EMA), enlarged from original: 1:50.000





**ስዕል ፱** የ"ሲሬ ከተማ" (መ፩-መ፫ = የከተማው መግቢያ/በር፤ ጉ፩-ጉ፭ = ጉድባዎች/ምሽጎች መግቢያ በሮችንና ጉብታውን ለመጠበቅ፤ ጥግ = ጥንድ የግምብ አጥር ቅንብር፤ ክግ = ክብ ግምብ፤ ፎ = በ "ላይኛው ከተማ" እና በ "ታችኛው ከተማ" መካከል፤ ወ = የወፍጮ ደንጋይ፤ ደ = ለታችኛው ከተማ ደጃፍ/በር፤ ግም = የግምብ አጥር ምሽግ ቅንብር፤ ሰም = ሰው ሠራሽ ምሽግ፤ ጅ = ጅረት፣ የቤልቤላን ወንዝ ሲጨመርበት፤ ትወም = የትኩስ ውሃ ምንጭ

**Fig. 9** – The "City of Sire" (E1-E3 City Entrances/Gates; B1-B5 Bastions/Fortifications to protect entrances & heights; R Double Wall structure; CW Circle Wall; T Tower between "upper city" & "lower city"; M Millstone; D Doorway/Gate to Lower City; WT Wall-Trench system; Tr Artificial Trenches; F Ford crossing Belbela river; FWS Fresh Water Spring)





**ፎቶ ፩** በወጨጫ የተራራ ሰንሰለት ላይ አንዣቦ ያለው ምሽግ ያለበት የጉብታ አናት

**Picture 1 –** The dominating fortified hill-top on the Wechecha Range.




**ፎቶ ፪** የወጨጫ የተራራ ሰንሰለት፤ በስተሰሜን በኩል ያለው ግዙፉ ከፊል የግምብ አጥር

**Picture 2 –** Wechecha Range: The massive Section Wall to the north




**ፎቶ ፫** የወጨጫ የተራራ ሰንሰለት፤ የውጩ የግምብ አጥር (በስተሰሜን በኩል ያለው)

**Picture 3** – Wechecha Range: Outer Wall (to the south)




**ፎቶ ፬**　የወጨጫ የተራራ ሰንሰለት፤ የውጩ የግምብ አጥር (በስተምዕራብ በኩል ያለው)

**Picture 4 –** Wechecha Range: Outer Wall (to the west)




**ፎቶ ፭** የወጨጫ የተራራ ሰንሰለት፤ የውስጠኛው ክብ የግምብ አጥር ከከፍል የግምብ አጥሩ ዕይታ ጋር

**Picture 5 –** Wechecha Range: The Inner Circle Wall with view of Section Wall




**ፎቶ ፮** የወጨጫ የተራራ ሰንሰለት፤ የከፊል የግምቡ አጥር፤ ከደሞጫ ተራራ ዕይታና ከፍል ገጽ ጋር (የተራራው ከፍታ ፴፰፻፹፭ ሜትር ከባሕር ወለል በላይ )

**Picture 6 –** Wechecha Range: Section Wall with view to and parts of Mt Dämoča (3885m asl)




**ፎቶ ፯** የጉብታ አናት የእንስላሌ ጢቆ ላይ ከ "ተደለደለ ደረጃ ምድር" ጋር

**Picture 7 –** Hill-top at Insilale Tiko with "terraces"




**ፎቶ ፰** እንስላሌ ጢቆ፤ በጉብታው አናት ላይ የጥንድ የደከጋይ ክቦች (በስተጀርባው በኩል፤ የከፍል የግምብ አጥሩ? ይሆን!)

**Picture 8 –** Insilale Tiko: Double stone circle on top of the hill (background: section wall?)




**ፎቶ ፱**  የኢቺቼ የተደለደለ ደረጃ ምድር የጉብታ አናት

**Picture 9 –** Terraced hill-top of Ichichie




**ፎቶ ፲** የ “ሲሬ ከተማ”፤ የግምብ ቅንብሮች ካለው የጉብታው አናት ላይ ያለው ዕይታ፤ ወደ ጨፌ ዶንሳ ከሚወስደው መንገድ፤

**Picture 10 –** “City of Sire”: View on the hill-top with wall structures from the road to Chefe Donsa




**ፎቶ ፲፩** የ “ሲሬ ከተማ”፤ የቤልቤላን ወንዝ የሚገጥመው ጅረት

**Picture 11 –** “City of Sire”: The ford crossing the Belbela river




**ፎቶ ፲፪** የ “ሲሬ ከተማ”፤ አለቱን በመጥረብ መንገድ የተወጣበት (በስዕሉ ማዕከለኛ ክፍል)

**Picture 12 –** “City of Sire”: Path cut into hill rock (middle of picture)




**ፎቶ ፲፫** የ “ሲሬ ከተማ”፤ የመግቢያ በሩ/ደጃፉ **መ፪** ከጅረቱ ወደ መግቢያ በር **መ፪** የሚወስዱ ደረጃዎች

**Picture 13 –** “City of Sire”: The entrance/door E2 with staircase leading from the ford to entrance E2




**ፎቶ ፲፬** የ “ሲሬ ከተማ”፤ በደቡብ በኩል የ “ታችኛውን ከተማ” ከጥቃት የሚከላከሉ እልም ያሉ ገደላማ ቁልቁለቶች (ፏፏቴው ከሥሩ ለጥቆ አለ)

**Picture 14 –** “City of Sire”: Steep precipices protecting the “lower city” to the south (the waterfall is just below)




**ፎቶ ፲፭** የ “ሲሬ ከተማ”፤ ከ “ታችኛው ከተማ” ደቡብ ምዕራብ ጫፍ ላይ፤ ለሶስተኛው መግቢያ በር ቅርብ ቦታ ላይ ያሉ ሰው ሠራሽ ምሽግ

**Picture 15 –** “City of Sire”: Artificial trench at the south western end of the “lower city” close to entrance B3




**ፎቶ ፲፮** የ “ሲሬ ከተማ”፤ ትልልቅ ተጠርበው የተዘጋጁ ለሕንፃ የሚሆኑ አራት ማዕዘን ያላቸው ጡቦች ( ፩ ተኩል፣ ነጥብ ፮፣ እና ነጥብ ፪ ሜትር ርዝማት፣ ስፋትና ቁመት ያላቸው ) ከጉብታ አናት ላይ (ጥግ - ጥንድ የግምብ አጥር ቅንብር)

**Picture 16** – “City of Sire”: Large extracted rectangular building blocks (1.5 x 0.6 x 0.2m) from the hill-top (R)




**ፎቶ ፲፯** የ “ሲሬ ከተማ”፤ የደንጋይ አቀማመጦች ከጥንድ የግምብ አጥር ቅንብሩ፤ መሠረቶችን ለማሳየት ይሆን?

**Picture 17** – “City of Sire”: Stone setting from R, indicating foundations?




**ፎቶ ፲፰** የ “ሲሬ ከተማ”፤ የወፍጮ ደንጋይ (ወ)

**Picture 18 –** “City of Sire”: Millstone (M)




**ፎቶ ፲፱** የ “ሲሬ ከተማ”፤ ወደ “ታችኛው ከተማ” መግቢያ ደጃፉ/በር (ደ)

**Picture 19 –** “City of Sire”: Doorway/Gate (D) to “lower city”



**ፎቶ ፳** የ “ሲሬ ከተማ”፤ የአንድ ጥንታዊ ግዙፍ የግምብ አጥር ቅንብር መሠረቶች፤ ከመግቢያ በር **መ፬** አጠገብ

**Picture 20 –** “City of Sire”: Foundations of an older massive wall structure close to E4



**ፎቶ ፳፩** የ “ሲሬ ከተማ”፤ በግዙፎቹ የግምብ አጥር አናት ላይ ቀለል ያሉ የግምብ አጥሮች

**Picture 21 –** “City of Sire”: Lighter wall structures on top of massive ones